# ትውስታዬ

በሚሊዮን በለጠ

ኤዲተር ወንድዬ ዓሊ

ራዕይ አሳታሚ

አዲስ አበባ 2010 ዓ.ም

# ትውስታዬ

በሚሊዮን በለጠ

ኤዲተር፡- ወንድዬ ዓሊ

የሽፋን ንድፍ እና ገጸ ውበት፡- ካሌብ በለጠ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

አሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ በከፊልም ሆ!
በሙሉ ማባዛት፣ በኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች መቅረጽና ማራባት የተከለከለ ነው።

ራዕይ አሳታሚ
ፖ ሳ ቁጥር 2332
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
RP-26





## አምላኬ ሆይ!

አንተ ከልጅነቴ ጀምረህ አስተምረኸኝ

ገና አሁንም ድንቅ ሥራህን እናገራለሁ

መዝሙር 71፥17

# መታሰቢያ

ላትጠግበኝ ተስላ ለሸኘችኝ፣

እማርላት ዘንድ ብርቱ እርምጃዎችን ለወሰደችው፣

ሳልጠግባት ለተለየችኝ፣

ለውድ እናቴ ለአፀደ ወልደ ሰንበት ትሁን





ማውጫ


መግቢያዎች 1

ምዕራፍ አንድ

- መነሻዬ 17
- አሃዱ - ስል 17
- ሲቀጥል 23
- ሦስቱ 38

ምዕራፍ ሁለት

- ወደ አካዳሚክ ሕይወት 42
- አዲስ ጅማሬ - በአዲስ አበባ 42

ምዕራፍ ሦስት

- የሥራ ዓለም 52
- በጅማ በር ራድዮ ጣቢያ 52

ምዕራፍ አራት

- የውጪ ዓለም ተሞክሮ 62
- ባህር ማዶ ለትምህርት 62
- ዝግጅትና ጉዞ 65
- ዋሸንግተን ዲሲ 70
- ዊሊያምስፖርት ቴክኒካል ኢንስቲትዩት 73
- ዌስተርን ሚሺጋን ዩኒቨርሲቲ 77
- ኢስተርን ሜኖናይት ኮሌጅ 80
- ወደ ኢትዮጵያ መልስ 82

ምዕራፍ አምስት

- ከትምህርት መልስ፦ ሥራ፣ ኑሮና ትዳር 85
- እንደገና ሃረርቲ 89
- ተግባረ ዕድ በመምህርነት 95

| | |
|---|---|
| አኔና ግደይ መግባባት ጨመረ | 96 |
| ሥርግ፤ ህልምም አውነትም | 102 |
| ድክ ድክ ወደ አገልግሎት፤ ቢሊግርሃም በአዲስ አበባ | 107 |
| **ምዕራፍ ስድስት** | |
| ዳግም ወደ አሜሪካ ከቤተሰብ ጋር | 108 |
| ዝግጅትና ጉዞ ወደ አሜሪካ | 111 |
| ኑሮ በአሜሪካና ትምህርት | 112 |
| መንፈሳዊ ሕይወት በአሜሪካ | 116 |
| **ምዕራፍ ሰባት** | |
| ወደ አገሬ መልስ | 118 |
| ሥራና አገልግሎት በመቀሌ | 119 |
| ኑሮ ሥራና አገልግሎት በባህርዳር | 129 |
| የአጼ ገላውድዮስ ት/ቤት ዲሬክተርነት | |
| አገልግሎት በናዝሬት | 137 |
| የፖሊቴክኒክ ኢንስቲቱት ዲሬክተርነት | 139 |
| የባህርዳር መንፈሳዊ አገልግሎት | 146 |
| ስለ አዲስ መንፈስ ቅዱስ አንቅስቃሴ | 151 |
| **ምዕራፍ ስምንት** | |
| መሠረተ ክርስቶስ ቤ/ክ አጀማመርና ተሳትፎዬ | 156 |
| በአለም ሜኖናይት ኮንፍረንስ ላይ ተሳትፎዬ | 162 |
| **ምዕራፍ ዘጠኝ** | |
| ከመንግስት መሥሪያ ቤት መለየት፤ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር | 168 |
| ሁሉንም ቤተ አምነቶች በማህበሩ ሥራ ማሳተፍ | 175 |
| የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ምስረታና ማጠናከር | 177 |







| | |
|---|---|
| የአለም መጽሐፍ ቅዱስ ማህበሮች ጠቅላላ ስብሰባ በአፍሪቃ አዳራሽ | 184 |
| **ምዕራፍ አሥር** | |
| በአፍሪቃ ደረጃ ማገልገል | 188 |
| የአፍሪቃን ማሕበሮች የማገልገል ዉጣ ዉረድ | 195 |
| ኑሮና አገልግሎት በናይሮቢ፤ የኢትዮጵያ ኮሙኒትይ በኬንያ | 205 |
| **ምዕራፍ አሥራ አንድ** | |
| ሕይወት በሽበት፤ ጡረታ መውጣት | 214 |
| ለኢትዮጵያ ምን ልናደርግ አንችላለን? | |
| የራዕይ መጻህፍት መደብርና አሳታሚ ድርጅት | 220 |
| የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት | 223 |
| **ምአራፍ አስራሁለት** | |
| ሌሎች አበይት ተሳትፎዎች | 232 |
| በወንጌላውያን አብያት ክርስቲያናት ሕብረት | 232 |
| በወርልድ ቪዥን፤ የተስፋ ድርጅት፤ አፍሪቃ ኢንተርፕራይዝ | 235 |
| ክርስትናና ፖለቲካ | 240 |
| የጤና መታወክ | 247 |
| **ምዕራፍ አስራሶስት** | |
| ኑሮ በአሜሪካና ሌሎች ተሳትፎዎች | 261 |
| የደስታ ቀኖች | 260 |
| መደምደሚያ | 265 |
| ቅድመ ኅትመት የአንባቢዎች አስተያየት | 268 |

# መግቢያዎች

## እንደ መግቢያ

ይህ መጽሐፍ የአንድ ሰው ታሪክ አይደለም!!! ይህ ዐረፍተ ነገር ምን ያህል እውነት እንደሆነ ማወቅ የሚቻለው ግን ይህንን መጽሐፍ በማንበብ ብቻ ነው። መጽሐፉ በአርትኦት አልፎ ለአትሞት ከመውጣቱ በፊት አፍታውን ቀምሼ "ለካ የአገርም ታሪክ በአንድ ሰው ታሪክ በኩል ሊነገር ይችላል" አልኩ፣ ይህንን አባባል አንባቢም እንደሚደግመው አልጠራጠርም።

የአውሮፓና የአሜሪካ ነጮች ጥቁሮችን በሚረግጡበት ዘመን ከኢትዮጵያ ገጠራማው ክፍል ከደደር ከተማ የአንድ ገበሬ ቤት ወጥቶ ገና በወጣትነቱ የአፍሪካ ቶመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ዋና ጸሐፊ በመሆን የጥቁር "አኩሪ" ለመሆን የበቃ ማን መሰላችሁ? ለፊው ዋርካ ጋሽ ሚሊዮን ናቸው። ጋሽ ሚሊዮን በዚያ በጠባቡ በሚኬድበት ዘመን እንዴት ቅርንጫፋቸው ሰፋ? ገና ከወጣትነት ጓደኞቻቸው ጋር ስለ ወደፊት ኑሯቸው ሲያስቡ ለአገር ብልጽግና ስለሚያበረክቱት ሙያ እንዴት አሰቡ? የእነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች መልስ የጋሽ ሚሊዮን ታሪክ የዘመን ጓዶቻቸውን (ኮንቴምፖ'ራሪስ) ሰፊ አስተሳሰብ ይጠቁመናል። መቼም ቢሆን ሰው ከትውልድ ዘመኑ ወደ ኋላ ሔዶ መወለድ አይችልም፣ ይሁን እንጂ ወደኋላ የተከሰቱትን የማወቅ ጉጉቱ ከፍተኛ ነው፤ ይህ ጉጉት ሊሟላ የሚችለው ደግሞ ከእኛ ዘመን ቀድመው የነበሩ ሰዎች በጥንቃቄ ዘመናቸውን ሲተርኩልን ነው፤ እነሆ ይህ መጽሐፍ እንዲህ ዓይነት ነው።

በዚህ መጽሐፍ ንባብ እንድ ሰው ለማንበብ መዘጋጀት ብቻ ሳይሆን ለጉዞም መዘጋጀት ያለበት፣ ከ"ሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት" ደደር ወረዳ አንስቶ የባቡር ሐዲድን ተከትሎ አዳማ በመግባት፣ ዓመታት በቆጠሩ መጠን በጥራትና በፍጥነት፣ የኢትዮጵያ ዋና ዋና ነባር ግዛቶች፣ ከዚያም ወደ ሰሜን አሜሪካ፣ ብሎም ወደ አፍሪካና ልዩ ልዩ የአውሮፓና የዓለማችን ክፍለ አህጉራት በጋሽ ሚሊዮን ታሪክ እየቀዘፉ መጓዝ ምንኛ ደስ ያሰኛል፣ በተለይ በጠበቧ የመኖሪያ

ስፍራ ሆነን ዓለም ይህችው ብቻ፣ ሰውም እኛው ብቻ፣ ሙያም የኛው ብቻ፣ ተሞክሮም የኛው ብቻ ለሚመስለን ይህንን መጽሐፍ ማንበብ የተሻለ ማያ ይሰጠናል፣ ስለዚህ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መቆየት ከአገር ሳይወጡ አለምን መዞር ነው ብዬ አምናለሁ።

ይህ መጽሐፍ ብዙ ሰዎችን ያስተዋውቀናል እድሜአቸው እንደ ጋሼ ሚሊዮን ሰማንያዎቹና ከዚያም በላይና በታች የሆኑ የእድሜ ዘለቅ ባለጠጎች የአፍላ ዘመን የባዶ አግርና የቁምጣ ለበስ ታሪካቸው በዚህ መጽሐፍ ውሰጥ ይወሳል፣ የአሁን ግዙፎች የትናንት ልጆች፣ ወጣቶች እንደነበሩም በግልጽ አናያለን በዚህ የትውስታ መጽሐፍ፣ አነ አርቲስት አገሌ፣ እነ ፕሮፌሰር አገሌ፣ እነ ሚንስትር እገሌ፣ አነ ክቡር አቶ አገሌ ሁሉ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ይነሳሉ፣ ለካ እንዲህ ነበሩ እንላለን። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን የምንጓዘው በጋሽ ሚሊዮን ትውስታ ውስጥ ነው!

ይህ መጽሐፍ የአንዳንድ አንጋፋ ድርጅቶችን የጅማሬ ታሪክ ያስተዋውቀናል፤ ስለ ቀድሞው የሬድዮ ጣቢያ ምን እናውቃለን? የተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት የቀድሞ ሥርአተ ትምህርት ምን ዓይነት ነበር? ሰዎች ድሮ ድሮ ወደ ውጭ አገር ለትምህርት ሔደው ለመመለስ የሚቸኩሉት ለምንድን ነው? የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ምን ይመስላል? አገራችን ኢትዮጵያ ለአፍሪካ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ያደረገችው አስተዋጽኦ ምን ነበር? የሚሉት ከብዙ በጣም ጥቂት ጥያቄዎች ናቸው፤ መጽሐፉ መልስ አለው። የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የጅማሬ ታሪክ በዙር ምስክር (የመጀመሪያ ተአማኒ) ለሚፈልጉ እነሆ ትውስታዬ በሚገባ ታቀርባለች።

ሰሎሞን ጥላሁን

(ከአሜሪካ ቨርጂኒያ)





## ጥቂት ቃል

ዱሮ ዱሮ በልጅነቴ ዘመን ተማሪ እያለሁ በተለይ በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበርሁባቸው አመታት የታሪክና የጅግራፊ ትምህርቶችን እጠላ ነበር። ለእነዚህም ትምህርቶች የምሰጠው ትኩረት በፈተና ሰሞን የሚያስፈልገውን ውጤት ብቻ ለማግኘት ያህል ብቻ ከመንደፋደፍ ዉጭ ከልቤ አጥንቻቸው አላውቅም። አንድም ሽምደዳን የምወድ ስላልነበርሁ በሌላም በኩል ወደ ሳይንስ ትምህርት አዘነብል ስለ ነበረ ነው።

ከብዙ አመታት በኋላ ግን ይህ አስተሳሰቤ ተለወጠ፤ ለታሪክ ተገቢውን ትኩረት ያስፈልጋል ወደሚለው መጣሁ፤ ለምን? ቢባል ከታሪክ ብዙ ጥቅም ይገኛልና። ስኬት፡ ክስረት፥ ድል፡ ሽንፈት፥ መልካም ሕይወት፡ አሳዛኝ ሕይወት፡ ዉጤታማነትና ዉጤት አልባነት. . . ወዘተ የመሳሰሉትን አይቶ ማገናዘብ የሚቻለው በታሪክ መስተዋትነት ነውና።

ብዙ ጊዜ “ከታሪክ የማይማር፣” ወይም "ከታሪክ አለመማር” ወይም “ከታሪክ መማር” የሚሉት ሐረጎች ተደጋግመው ይነገራሉ። ትክክል ነው፤ ግለሰብ፥ ማኅበረሰብ፥ ቤተ ክርስቲያን፣ ሕዝብ ወዘተ፣ በታሪክ መስተዋት ያለፉበትን ሁሉ እያዩ ስህተትን ከመድገም ይጠበቃሉ። አልፎም ወደ ስኬት ጎዳና ወይም ወደ ድል ጎዳና ያመራሉ፤ ወደ ውጤታማነትም ያቀናሉ።

የዕብራውያን ጸሐፊ ስለ ቀደሙት የእምነት አባቶች ከተረከ በኋላ እኛም እነርሱን ተከትለን የእምነት ተጋድሎ እንድናደርግ (በምዕራፍ 12) ይመክረናል። በመጽሐፍ ቅዱስ የድልና የስኬት የጽድቅ ታሪኮች አሉ። በአንጻሩም ብዙ የሽንፈት፥ የውድቀት፥ የርኩሰት ታሪኮችም አሉ። ሁሉም ግን የተጻፉልን ሕይወታችንን ለፍጹምነትና ለበጎ ሥራ እንድናዘጋጅ ነው።(ጢሞ. 3፥16-17)

አቶ ሚሊዮን የትውስታውን ረቂቅ እንዳነብ ሲጠይቀኝ የተቀበልኩት በደስታ ነው፤ ከወንድሜ ከሚሊዮን በለጠ ጋር በክርስቶስ ለ63 ዓመታት ተቋርጦ የማያውቅ የዘለቀ ጓደኝነት አለኝ። ከሕይወቱ ብዙ መልካም ነገሮች ተምሬአለሁ፤

በእውነት ጌታን የሚወድ ህቀኛ ሰው ነው። በክርስቶስ ያሰንን ወዳጅነት የቦታ ርቀትም ሆነ በተሰያዩ ቦታዎች መኖር አልተፈታተነውም።

በ1960ዎቹ አመታት እርሱ በናይሮቢ እኔ በአሰብ እያሰሁ ብዙ ደብዳቤዎች ተሰዋውጠናል፤ በአንድ ወቅት ሰጻፈልኝ ደብዳቤ ቶሎ መልሰ ሳልሰጥ በመቅረቴ ከአርሱ የደረሰኝ ደብዳቤ የሚከተሰውን ሐሳብ የያዘ ነበር፤ "ምናልባት ደብዳቤዬ በመንገድ ተጠልፎ ቀርቶ ከሆነ ይሄኛውን ደብዳቤ ማንበብ የሚፈልግ ካለ አንብቦ እንዲያስተላልፈው ይሄው ሳሳሸግ ልኬልሃለሁ" የሚል ነበር። እነሆ ወገኖቼ ዛሬም ወንድሜ ሚሊዮን እግዚአብኄር ያደረገሰትን "ትውስታዬ" ብሎ በሰየማት ታሪኩ በግልጽ ያሳየናል፤ ከሰህተቱና ከውድቀቱም እንድንማር ምንም ሳይሰውር ጽፎልናል። ስሰዚህ ወንድም ጌታን እያከበርን ያበረከተልንን ብናነብ እናተርፋሰን።

ማሞ ገብረ መሰቀል

(የኢትዮያ ቃሰ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የቀድሞ የቦርድ ሰብሳቢ)





## የማውቀውን ሰው እንደገና የማወቅ ያህል

ጋሽ ሚሊዮንን ሰረጅም ዘመናት በቅርብ ሰማወቅ ዕድል ካገጠማቸው ሰዎች መካከል አንዱ በመሆኔ እጅግ በጣም ዕድለኛ ነኝ።

ጋሽ ሚሊዮንን በደንብ "አውቀዋለሁ" ብዬ የማምን ሰው ነበርኩ። የሕይወት ታሪኩን የያዘችውን "ትውስታዬ" በሚል ርእሰ ያዘጋጀውን መጽሐፉን ረቂቅ ካነበብኩ በኋላ ግን፣ ከዚህ በፊት ስሰ እርሱ የነበረኝ ዕውቀት እጅግ በጣም አነስተኛ እንደነበረ ተገነዘብኩ። "ትውሰታዬ" እርሱን የመሰለ ወንድም የሰጠንን ጌታ እጅግ በጣም እንዳመሰግነው ምክንያት ሆናኛለች።

በግሌ ግን ጋሽ ሚሊዮን ለእግዚአብሔር መንግሥት የሠራቸውንና የፈጸማቸውን ታላላቅ ሥራዎችን ስመለከት፣ እንደ አቅሚቲ "ጌታን ሰረጅም ዘመናት አገልግያለሁ" ብዬ የማስበውን እኔን በጣም ያሳፈረችኝ መጽሐፍ ሆና አገኘኋት፡፡

ጋሽ ሚሊዮን ወደ ጌታ ከመጣበት ዘመን ጀምሮ፣ አሁን እስካለበት የዕድሜ ዘመን ድረስ የፈጸማቸው ወይም የሰጣቸው አገልግሎቶች እኔን ያስደነቀኝ በመሆኑ፣ ይህቺን መጽሐፍ የሚያነቡ ሰዎች ሁሉ በግልጽ እንዲያዩት ለቅሜ ከዚህ በታች አስፍሬያቸዋሰሁ፣

- የመቀሌ ጸሎት ቤት ጀማሪ ነበር፤
- "ብርሃን መጽሐፍ መደብር" የሚል ስያሜ የተሰጣትን የመጀመሪያዋን የመንፈሳዊ መጽሐፍ መደብር በመቀሌ አቋቋመ።
- የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርሰቲያን እንድትመሠረት ጌታ ከተጠቀመባቸው ወንድሞች ነው። "የመጀመሪያው የመሠረተ ክርሰቶስ መጋቢ ሆኜም ተካንኹ።"
- በባሕር ዳር መንፈሳዊ አገልግሎትን ጀመረ። - "መቀሌ እንዳደረግሁት ቤት ተከራይተን የጸሎት ቤት አንከፈት ብዬ ነበር። የሚከራይ ቤ ባሰማግኘታችን ቻፕል አሠራሁ።"

- መሠረት ክርስቶስ በማኅበር ከተደራጀች በኋላ የመጀመሪያዋ የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ መንበር ሆኖ አገለገለ።
- በኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር አማካሪ ቦርድ አባል እንዲሆን ተመረጠ።
- የኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ዋና ጸሐፊ ሆኖ አገለገለ።
- የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ሕንጻን አስርቶ አስመረቀ።
- የዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበሮች ጠቅላላ ለብሰባ በአፍሪካ አዳራሽ አስተናገደ።
- የአፍሪካ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበሮች ዋና ጸሐፊ ሆኖ አገለገለ።
- በናይሮቢ በአማርኛ የአምልኮ ፕሮግራም መጀመር ምክንያት ከሆኑት አንደኛው ነበር።
- በኬንያ የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ማህበር መስራቾች አንዱና ሰብሳቤ ሆኖ አገሰገለ።
- የራዕይ መጽሐፍት መደብርና አሳታሚ በኢትዮጵያ እንዲከፈትና አገልግሎት እንዲሰጥ አደረገ።
- በቢሊግራሃም የዓለም አቀፍ የሳታላይት አገልግሎት አስተባባሪ ሆኖ አገለገለ።
- የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት የዕርቅና ሰላም ኮሚሽን አባል ሆኖ አገሰገለ።
- የኢትዮጵያ ወርልድ ቪዥን የቦርድ አባል ሆኖ አገልግሏል።
- የተስፋ ድርጅት የቦርድ አባል ሆኖ አገሰገለ።
- የአፍሪቃ ኢቫንጀሊካል ኢንስቲትዩት ቦርድ አባል ሆኖ አገልግሏል።





- አነስተኛነቷን እንኳን ሳይንቅ፣ እኔ የምመራውን የወንጌል አገልግሎት በኢትዮጵያ ላለው እንቅስቃሴያችን የቦርድ ሊቀ መንበር ሆኖ አገልግሏል።

"ትውስታዬ" የሚለውን የጋሽ ሚሊዮንን የሕይወት ታሪክ የያዘችውን መጽሐፍ ለመገምገምና አስተያየት ለመስጠት ያልተቸገርኩት፣ ጋሽ ሚሊዮንን በረጅም ዘመን የማውቀው በመሆኔ፣ በብዙ አቅጣጫ ሕይወቴን ከነኩት ሰዎች መካከል አንዱ በመሆኑ ነው።

የቀድሞው ወንጌላዊው ማኅበረሰብ አባላት ጋሽ ሚሊዮንን የምናያይዘው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ነው። ጋሽ ሚሊዮን መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈ ሰው አይደለም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በብዙዎች እጅ እንዲገባ ምክንያት የሆነ ሰው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በቀላል ዋጋ ለሰዎች ሁሉ እንዲደርስ ያደረገ ሰው ነው::

በግሌ አንድ ትውስታ አለኝ:: እኔ ጌታን ባወቅሁበት ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ ዋጋ ብር 2.50 ነበር። ይሄም ሆኖ፣ ብር 2.50 የማግኘት አቅም ስላልነበረኝ፣ የራሴ የሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በእጄ የሚገባበትን ቀን በተስፋና በጉጉት እጠባበቅ ነበር።

ይህ ምኞቴ እውን የሚሆንበት ጊዜ ደረሰ። በአንድ ወቅት ትምህርት ቤት ሊዘጋ፣ ኤስ. አይ. ኤም. (S.I.M) ሁለት ሳምንት የሚቆይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሰወጣቶች አዘጋጅቶ ነበር። በመጀመሪያው ቀን ስለ ትምህርቱ መግለጫ ሲሰጥ፣ ሁለቱን ሳምንት ሳይቀር ሰሚመጣ ተማሪ "የመናኝ ጉዞ መጽሐፍ እና፣ እንዲሁም 500 ጥቅስ በቃሉ ላጠና ተማሪ መጽሐፍ ቅዱስ" እንደሚሸለም ገለጻ ተደረገልን። ያ ስናፍቀውና ስጓጓለት የነበረው ፍላጎቴ የሚሟላበት ጊዜ አንደ ደረሰ ተሰምቶኝ በደስታ ፈነደቅሁ። በዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ 500 ጥቅስ በቃል ማጥናት ቀላል ባይሆንም፣ ከነበረኝ ኃይለኛ ፍላጎት የተነሳ የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱሴ በእጄ እንደሚገባ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ አልነበረኝም። 500 ጥቅሶች በወረቀት ታትመው ተሰጠን። ከእኔ በስተቀር 500 ጥቅስ ለማጥናት የደፈረ ልጅ አልነበረም።

ከግማሽ ቀን በላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ ስለሆነ፣ ከቀኑ የምትቀረን ጊዜ በጣም ትንሽ ስለሆነች፣ ሌሊቱን ሳጠና አድር ነበር። በፕሮግራሙ መጨረሻ ቀን ለመጽሐፍ ቅዱስ የነበረኝን ጥማት የተረዳ ጌታ ረዳኝና ያጠናሁትን 500 ጥቅስ በአስተማሪዬ ፊት ቆሜ አንበለበልኩት። የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱሴና እንዲሁም "የመናኝ ጉዞ" መጽሐፍ በእጄ ገባ። እነዚህ ሁለት መጻሕፍት ናቸው የመንፈሳዊ ሕይወቴን የቀረጹልኝ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያቺ መጽሐፍ ቅዱሴ ለረጅም ጊዜ ከእጄ አልጠፋችም። በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች መካከል በተደረገው የመጽሐፍ ቅዱስ ውድድር አሸናፊ ሆኜ እስራኤል አገር የአንድ ወር ጉብኝት እንዳደርግ ዕድል ሰጠችኝ። በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ሰበከሁበት።

ያቺ በብዙ ትጋት ያገኘኋት የመጀመሪያዋ መጽሐፍ ቅዱሴ ከእኔ ጋር ብዙ ቆይታ፣ በ1959 ዓ.ም. በእሳት ተቃጠለች።

ታሪኳ እንዲህ ነው። የንግድ ሥራ ትምህርቴን ጨርሼ ባለደመወዝ ሆኜ ነበር፤በአንድ እሁድ ወንጌልን ለመስበክ ያቺን የመጀመሪያዋን መጽሐፍ ቅዱሴን ይዤ ወደ ደብረ ዘይት በሎንቺና ተጓዝኩ። ፕሮግራሙ ልክ እንደ ተጀመረ፣ የከተማው ሕዝብ "መጤ ሃይማኖትን ማጥፋት አለብን" በማለት ተነሳስተው የግቢውን አጥር ከንቾ እየመዘዙ ደበደቡን። ያቺም በብዙ ትግል ያገኘኋት መጽሐፍ ቅዱስ ከእጄ ወድቃ በእሳት ጋየች።

ሠራተኛ ስለነበርኩ እርሷን ለመተካት ይህን ያህል አልተቸገርኩም። ይሁን እንጂ፣ ገንዘብ በማጣት መጽሐፍ ቅዱስን በእጃቸው ለማስገባት የሚቸገሩ ብዙዎች እንዳሉ በማሰብ በገንዘብም፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር አባልና የቦርድ አባል በመሆን እስተዋጽዖዬን ለመፈጸም ሙከራ አድርጌአለሁ።

በዚህ ዓይነት መጽሐፍ ቅዱስን በእጃቸው ለመያዝ እቅም ለሌላቸው ሰዎች እንዲደርስ በማድረጉ ጋሽ ሚሊዮን ለብዙዎቻችን ባለውለታችን ነው።

ከዚህ በላይ መዘርዘሩ በመጽሐፍ ላይ ሌላ መጽሐፍ መጻፍ ይሆንብኛል።

መለሰ ወጉ





## ጥቂት ቃል ስለ ጋሽ ሚሊዮን

ትዉስታዬ በተሰኘዉ መጽሐፉ ጋሼ ሚሊዮን በለጠ ከልጅነቱ እስከ ሽበት ማውጣት የተሸከመው ጌታ ያደረገልትን ዋና ዋና ጉዳዮችን እያወሳ ሊያስነብ ቀርቧል። በጠቅላይ ልብ አንጠልጣይ ነው። ከትንሽ ጅማሬ ተነስቶ ትልልቅ አበይት የሆኑ ከንዉኖችን እንዲያደርግ የረዳውን ጌታ እጅና ምሪቱን በሕይወቱ አይቼበታለሁ። የሚከተሉት ዋና ዋና መሪ ቃላት የመጽሀፉን ቁም ነገሮች ለማስጨበጥ የተረዳሁትን ከዚህ በታች አቀርባለሁ።

### ለማወቅና ለመማር የነበረው ጉጉት

ጋሼ ሚሊዮን ፊደል ከቆጠረበት እለት ጀምሮ ተጨማሪ እውቀት ለማግኘት ከቄሶች፥ ከሃይማኖት አበው መምህራን፥ ከሞራል መምህራን በተለይ ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ ብርቱ ጥረት አድርጓል፤ ከዚህም የተነሳ ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ፥ እውንትን ለመረዳት በመፈለጉ ጌታ እራሱን ሊያውቀው ወደሚችልበት ወደሚችልበት ቦታ አድርሶታል፤ በናዝረት የድሬሰርና የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ከዚያም በአዲስ አበባ ተግባረዕድ ት/ቤት በነበረበት ወቅት ወደ ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ወደ ሚሰጡበት ቦታዎች በተለይም የሜኖናይት ሚሲዮን ያኪያሂደው በነበረበት ወደ መርሃ እውራን ት/ቤት በመሄድ ጌታን ሊያውቅ ወደሚችልበት አቋም መጥቷል።

በተጨማሪም ለመማርና ለማወቅ በነበረው ጥረት በአዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ት/ቤት ከክፍሉ የላቀ ዉጤት በማምጣቱ ተሸላሚ አድርጎታል። ወደ ሥራም በመሰማራቱ በቴሌኮሙኒኬሽን መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ጥቂት ወራት ከሠራ በኋላ በተማረበት በተግባረ ዕድ ት/ቤት ለማስተማር በቅቷል።

እግዚአብሔር የተለመለት እቅድ ስለነበረ የመንግስት ስኮላርሺፕ አግኝቶ ወደ አሜሪካን አገር በመሄድ ትምሯል። አሜሪካም በነበረበት ወቅት ከሜኖናይት ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠሩ በክርስትና ሕይወቱ

የበለጠ እየጠነከረ መሄድ ችሏል።

የሄደበትን ትምህርት እንደ ጨረሰ ተመልሶ በተግባረ ዕድ ት/ቤት ለሁለት አመት ካስተማረ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ስኮላርሺፕ አግኝቶ ወደ አሜሪካ በመሄድ በጀመረው የኤሌትሮኒክስ ሙያ ትምህርቱን ከተከታተለ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ በመመልሰ የማስተማር አገልግሎቱን ቀጠለ።

### የአስተዳደር ችሎታው

ጋሼ ሚሊዮን አሜሪካን አገር ተምሮ ከተመለሰ በኋላ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ወደ መቀሌ መጥቶ በአጼ ዮሐንስ ት/ቤት እያስተማረ የቴክኒክ ክፍሉን አደራጅቷል። በዚያን አመት እኔ በዛ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪ ነበርሁ። መቀሌ በነበረበት ጊዜ ቻፕል ከፍቶ ወንጌል ይሰብክ ነበር፤ በዚያ ጸሎት ቤት ይካፈሉ የነበሩት ፀሐይነሽ ኃ/ሥላሴ እና የተካ ገብሩ ባለቤት የሆነቺው ሳባ ተ/ሃይማኖት የክፍል ጓደኞቼ ነበሩ:: እኔም የእግዚአብሔር ቃል የማወቅ ጉጉት ስለነበረኝ መጽሐፍ ቅዱስ ገዝቼ ማንበብ ጀመርኩ። በዚያ ጋሼ ሚሊዮን በከፈተው ጸሎት ቤት ይካፈሉ የነበሩ እኔ የማውቃቸው ተማሪዎች ነጭ መብሩቅ ልብስ አሰፍተው ይለብሱ ነበር፤ ሲወጡም ሲገቡም ወደ ሻይ ቤት ሲሄዱ በአንድ ላይ ይተሙ ነበር:: ጋሼ ሚሊዮን ይሰብክበት በነበረው ጸሎት ቤት የእነዚህ ተማሪዎች ሕይወት መለወጡን አስታውሳለሁ፤ ይህ ሊሆን የቻለው ጋሼ ሚሊዮን ወንጌልን ለማካፈል በነበረው ጥረት እንደሆነ አውቃለሁ::

ጋሼ ሚሊዮን ይህንንም በባህር ዳር ፖሊተክኒክ ኢኒስቲትዩት አስተማሪና ዲሬክተር በነበረበት ጊዜ ደግሞታል፤ በዚያ ቻፕል አሠርቶ እንደነበረና ብዙ የፖሊቴክኒክ ተማሪዎች ጌታን እናዳወቁና ሕይወታቸውም እንደተለወጠ ይታወቃል። እርሱ ከእዛ ከለቀቀ በኋላ የከተማዋ ቀላውስት ባደረሱት ስደት ያሰራት ቻፕል እንደ ፈረሰች ከአዲስ አበባ ለወንጌል አገልግሎት ወደ እዚያ





ሄደው የነበሩት ተደብድበው ወደ አደስ አበባ እንደ ተመለሱ ይታወቃል:: ጋሼ ሚሊዮን እዛ በነበረበት ጊዜ ጌታን ያወቁ፣ በክርስትና ሕይወታቸው የበረቱ፣ እንደ ጋይም ከብረአብ፣ ተጋ ሳንዴዶ፣ ካሳ እጋፋሪ፣ ፈቃዱ አፍጋ፣ ፍቅሩ ዘለቀ፣ ታምሬ ኩያሞ . . . ወዘተ ይገኙበታል። እነኚህ ሁሉ የጋሼ ሚሊዮን ፍሬዎች የቤተ ክርስቲያን አገል ጋዮች ናቸው።

### ከፍተኛና የቤተ ክርስቲያን ተቋማት አስተዳደርና ማማከር

በመጽሐፉ በሰፊው እንድምናየው በቤተክርስቲያናችን መቋቋምና ምስረታ ታላቅ ሚና ተጫውቷል። የመጀመሪያው የኢትዮጵያ መጽሀፍ ቅዱስ ማህበር ዋና ጸሃፊ በመሆን ማህበሩን አደራጅቷል።የተባበሩት የዓለም መጽሐፍ ቅዱለ ማህበሮች አባል እንድትሆን አድርጓል፤ የተለፋ ድርጅት መስራች አባል ከመሆኑም በላይ የመጀመሪያው ቦርድ ሰብሳቢ፥ በወርልድ ቪዥን፣ በአፍሪቃ ኢቫንጀሊስቲክ ኢንተርፕሪዝ የቦርድ አባል በመሆን አገልግሏል።

### አለም አቀፍና አህጉራዊ አገልግሎት

የማማከርና የማስተዳደር ችሎታውን ያካበተው በመጀመሪያ በአፍሪቃ ሜኖናይቶች ኅብረት ከዚያም በዓለም አቀፍ ሜኖኒይቶች ኮንፍረንች ም/ፕሬዚዳንትነት በድኋላም በፕሬዚደንትነት በማገልገሉ ነው። በተጨማሪም የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር አመራሩ ባሳየው ችሎታው ለአፍሪቃ መጽህፍ ቅዱለ ማህበሮች ዋና ጸሃፊነት ተመርጦ በዚህ ግዙፍ በሆነው ድርጅት ቤቱን ናይሮቢ አድርጎ የአፍሪቃን መጽሐፍ ቅዱለ ማህበሮች መርቷል። ያቋቋማቸውም ማህበሮች አሉ።

ናይሮቢ በነበረበት ወቅት ከሌሎች ወንድሞች ጋር በመሆን የኢትዮጵያውያን ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያን አቋቁመው ህብረቷ በተለይ ለብዙ ኢትዮጵይውያን ስደተኞች መጽናኛ መሆንዋን ብዙዎች ይመሰክራሉ።

## አባትነቱ

ጋሼ ሚሊዮን በመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረትና አጀማመር ላይ ሚና ነበረው። ከሚሲዮናውያን አመራር ወደ ኢትዮጵያውያን የአስተዳደር ሽግግር ወቅት ከተሳተፉት አንዱ ነበር፤ እንዲያውም የመጀመርያው ክህነት የተሰጠው በኢትዮጵያ አባባል "ቄስ" ነበር። የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያኗ ኢትዮጵያዊ ሊቀ መንበር ሆኖ ሲያገለግል ነበር፤ የቤተ ክርስትያኒቱ ስም የተሰየመው እርሱ ሊቀ መንበር በነበረበት ጊዜ ነበር

ጋሼ ሚሊዮን በረጅም ጊዜ አገልግሎቱ ባካበተው እውቀትና ችሎታ የአስተዳደር ልምዱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደ አባት ይታያል እላለሁ:: ምክሩ የማለታረቅ አገልግሎቱ፣ አቅጣጫ ለማስያዝ ያለው ብቃቱ የአባትነት ክበሬታ ሲያንሰው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ይላል፤ "ምንም እንኳን በክርስቶስ ብዙ መሪዎች ቢኖሯችሁም ብዙ አባቶች ግን የሏችሁም ፤ እኔ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ወልጄአችኋለሁ፤" (1ኛ ቆሮ. 4፥15) መልካም መካሪ አቅጣጫ የሚያስይዝ፥ የሚያስታርቅ አባት በመካከላችን የመኖሩ አስፈላጊነት አጠያያቂ ባይሆንም አንድ አባት ግን ነበረን፤ እርሱም ጋሼ ሚሊዮን በለጠ ነው።

ከዚህ ጋር አያይዤ ልል የምፈልገው እንደምሳሌ ሊታይ የሚገባን በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የቆዩት መሪዎች እርስ በርስ ያላቸው ቤተሰባዊ መቀባበል እጅግ የሚያስደስትና የሚያስቀናቃም ነበር:: እነዚህ መሪዎች በሃዘን ሆነ በደስታ ጊዜ አይለያዩም፤ የቤተ ክርስቲያን አባላቸው ሲታመም ሆነ ቢሞት ተሰብስበው አብረው ይሆናሉ፥ ሃዘን ይካፈላሉ፥ ያስቀኑኛል። ምነው እኛ የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን ነካን እላለሁ፤ ይህ የሚያስቀና ህብረታቸው በሌሎች ቤተ ክርስቲያን ሊቀሰምና በሥራ ላይ ቢዉል ከብዙ የማያስፈልግ ኪሳራ መዳን በተቻለ ነበር፤ ብዙ ምክር ባለበት አሰራር ውብ ይሆናል።

ሳልገልጸው የማላልፈው ጋሼ ሚሊዮን ስለ ልሳንና በሕዝብ መሐከል ስለመናገር ያለውን ነው፤ በእርግጥ ሥርአት በማጣት በግድየለሽነት የሚደረግ ነገር ሐዋርያው





ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ በሰፊው በ1ኛ ቆሮንቶስ 14 ሁሉ ነገር በአግባብና በሥርአት ይሁን ብሏል፤ በልሳን የሚናገር የማይተረጎም ከሆነ ምንም ጥቅም የለውምና ዝም ብሎ በራሱና በእግዚአብሔር መሃከል ያድርገው ይላል፤ ሌሎችን ማደናገር ስለሆነ በመድረክ ላይ ቆሞ በልሳን መናገር ትክክል አይደለም እላለሁ፥ እኔም ለሰባኪዎችና ለፕሮግራም መሪዎች በዚህ ጉዳይ ጥንቃቄ ቢያደርጉ በተለይ 1ኛ ቆሮንቲስ 14ን ደጋግመው ቢያነቡ ጥሩ ነው እላለሁ፥ አግረመንገዴን።

## የትዳር ሕይወት

ጋሼ ሚሊዮን በለጠ ከትዳር አጋሩ ጋር ሃምሳ ስምንት አመት በላይ የዘለቀ የአምስት ወንዶች ልጆችና አንዲት ሴት ልጅ አባትና የልጅ ልጆችም አሉት፤ የትዳር ሕይወቱ ምሳሌነቱም ቀላል አይደለም።

## የፖለቲካ ተሳትፎ

ጋሼ ሚሊዮን በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሕይወት ለመሳተፍ ጥረት አድርጓል፤ ክርስቲያን በፖለቲካ መሳተፍ አለበት ከማለቱም በላይ ምን ያህል በሃገር ላይ ተሳትፎ ለማድረግ መፈለጉን ያመለክታል፤ በምርጫ ከሌሎች አባላት ጋር አሸናፊ ሆኖ ቢወጣም ተሳትፎበት የነበረው የፖለቲካ ድርጅት በመፈራረሱ ሳይሳካለት ቀረ።

### ሕመሙ

ጋሼ ሚሊዮን የእድሜ ባለጸጋ ቢሆንም የተለያዩ ሕመሞች ገጥመውታል፤ በእነዚህም ግዚያት ሁሉ ጌታ እልጋውን ስላነጠፈለት በትዕግስት ጌታን በመጠበቁ በሕይወት ቆሞ ለመሄድ ችሏል። ከካንሰር፥ የወገብ ሕመም፥ የትሪፕል ፓስ የልብ

ቀዶ ጥገና ተደርጎለት ማለፉ የእግዚአብሔር ፀጋ ረድቶት ዛሬ ቆሞ ይሄዳል፤ ይህ የጌታ እጅ በእርሱ ላይ እንዳለ ያመለክታል።

## የራዕይ ማሳተሚያና መጻሕፍት መደብር ድርጅት

ለ19 አመታት በናይሮቢ ቆይታው በዚያ ከነበሩት ክርስቲያን ወንድሞች ጋር በመሆን በኢትዮጵያ የመጻህፍት ማሳተሚያና ማከፋፈያ ድርጅት ለመክፈት አቅደው "ራዕይ መጻሕፍት መደብርንና ማሳተሚያ ድርጅትን" አቋቋመዋል፤ ይህ ድርጅት እንደኔ ላለው ለማሳተም አቅም ለሌለው ሁለት መጻህፍት አትሞ አለራጭቶልኛል፤ በክርስቲያኑ ዘንድ መጽሐፍ የማንበብ ባህል እንዲጎለብት ጥረት አድርጎአል፥ እያደረግም ነው፤ የዚህ ድርጅት መቋቋም በጋሼ ሚሊዮን ጥረት የተገኘ ነው።

እንግዲህ "ትውስታዬ" የተሰኘው የጋሼ ሚሊዮን በለጠ መጽሐፍ ብዙ ቁም ነገር የያዘ ስለሆነ በጥሞና እንድታነቧት አሳስባለሁ፡፡

ጌታ ማስተዋልን ይሰጠን፡፡ ጋሼ ሚሊዮን ወደ ጌታ ሄዶ ቢሆን ኖሮ ይህቺን መጽሀፍ አቧራ አፈር ተጭኗት ነበር፤ አንድ ሰው ወደ ቀብር ቦታ ሄዶ ከጎበኘ በኋላ እንዲህ አለ ይባላል፤ "በዚህ መቃብር ሥፍራ ብዙ ያልተጻፉ ድርሰቶችና መጻሕፍት ተቀብረዋል"።

እንግዲህ ይህ ትውስታዬ መጽሐፍ በሕይወት ያለነውን የየራሳችሁን ትውስታ በመጻፍና በማሳተም ለትውልድ ቀሪ ነገር ልንተው ይገባል እላለሁ። መልካም ንባብ ይሁንላችሁ።

በድሩ ሁሴን





## መቅድም

ይህ መጽሐፍ ልዑል እግዚአብሔር በሕይወት ዘመን ጉዞዬ ባደረገልኝ መለኮታዊ ጥበቃው፣ ምሪቱና ከከፈተልኝ የሥራና የአገልግሎት በሮች መካከል ጥቂቶቹን ብቻ ለመዘከር ያህል ትውስታዎቼን አሰባስቤ ላለውና ለሚመጣው ትውልድ ለመመለከር ያደረግኹት ሙከራ ውጤት ነው፡፡ ርዕሱን "ትውስታዬ" ያልኩት ይኹነኝ ብዬ ነው፤ ምክንያት አለኝና፡፡

ሚሊዮን በለጠ የሚባለው ሰው ገና ብላቴና ሳለ ለያውቀው የሚያውቀው እምላከ፡- ከሃይማኖተኝነት ወደ ወንጌል አማኝነት፣ ከእረኛ በትር ወደ ቀለም ብዕር፣ ከጥብቆ ለባሽነት ወደ ባንጠሎን ታጣቂነት፣ ከከብት እረኝነት ወደ መሪነት፣ ከየኔታ ፊደል ቤት - ወደ ኮሌጅ ተማሪነት፣ ከመንደር ደብተራነት ወደ አደባባይ ሰውነት፣ ከብሔራዊ አገልጋይነት ወደ ዓለም አቀፍ ኃላፊነት... ወዘተ አሸጋገረው፡፡

እንዲህም ከሆነ ባለታሪኩ ሰውዬው ሳይሆን እግዚአብሔር ነው፡፡ የኔ ድርሻ ከትውስትዎቼ መካከል ዋና ዋናዎቹን ብቻ መርጬ በጽሑፍ ማስፈር ነበር። የታሪኬ ጀማሪና መደምደሚያ የሆነውና ከልጅነት እስከ ሽበት ተሸክሞ እዚህ ያደረሰኝ እግዚአብሔር መሆኑን ስለ ምገነዘብ "ታሪኬ" ከማለት ይልቅ "ትውስታዬ" ማለቱ የተሻለኝም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡

የዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማ ያለውና የሚመጣው ትውልድ ከድካሜም ሆነ ከብርታቴ ይማር ዘንድ ስለሆነ በተቻለኝ መጠን በሕይወት ዘመኔ ያሳለፍኳቸውን ዝንጋታዎቼና መደናገሮቼን ሁሉ ለማካተት ሞክሬአለሁ፡፡

አንዳንዶቹ የዋኅ አድራጎቶቼ ለአዲሱ ትውልድ ቂልነት መስለው ይታዩ፣ ምናልባትም መቀለጃ ሊሆኑ እንደሚችሉ እየተገነዘብኹ ነው የጻፍኳቸው። ይሁን እንጂ አንባቢዎች ከሃምሳና ስልሳ ዓመት በፊት የነበረውን ትውልድና ጠቅላላውን ዐውድ ወደ ኋላ መለስ ብሎ ለማየት እንደሚረዳቸው አምናለሁ።

ትውስታ ነውና ዓመታት በተቆጠሩ መጠን፣ የእንዳንድ ሰዎች ሙሉ ስም፣

ዓመቱና ልዩ ሥፍራው ተዘንግቶኝ ቢሆን በቅድሚያ ይቅርታ። በተጨማሪም በትውስታዬ የጠቀስኳቸው ብዙ ቢሆኑም ያልጠቀስኳቸሸው ብዙ ዘመዶችና ጓደኞች መኖራቸውን ልጠቁም እሻለሁ።

መልካም ንባብ

ሚሊዮን በለጠ።





# ምዕራፍ 1

## መነሻዬ

### አሃዱ - ስል

በቤተሰቡ ውስጥ ደስታ ሰፍኗል፡፡ ደስታው ወ/ሮ አፀደ ወልደ ሰንበት ለአቶ በለጠ ወልደ ገብርኤል ግንቦት 22 ቀን 1925 ዓ.ም ልጅ ምውሰዳቸው ነበር፡፡ ለቤተሰቡ ልጅ ሲወለድ የመጀመሪያ አልነበረም ከዚህ በፊት አስገደች የተባለች ሴት ልጅ ተወልዳለች፡፡ በአሁኑ ግን ወንድ ልጅ ተወልዷልና በቤተሰቡ ዘንድ ደስታና ሃሴት ሰፍኗል፡፡

ወንድ ልጅ መወለዱ ያስደሰታቸው የቤተዘመድ አባላት ስም ለማውጣት ተሽቀዳደሙ፡፡ የአቶ በለጠ እህት ዘነበች "መሊሆን" ይባል አለች፡፡ ምክንያቱም በዚያን ወቅት በአውራጃው ከተማን ከከተማ የሚያገናኝ መንገድ ያሠሩ "ፊታውራሪ መሊሆን" የሚባሉ በሕዝቡ ዘንድ የተወደዱ የወበራ አውራጃ ገዥ ነበሩ፤ እነሆ ለያሜው ሁሉንም ሰው ያስደሰተ ሆነ፤ ሕፃኑ "መሊሆን" ተብሎ ተሰየመ፡፡ መሊሆን ማለት እኔ ነኝ፡፡

አክስቴ ስም በማውጣት የተዋጣላት ነበረች ማለት ይቻላል፡፡ ከእኔ ቀጥሎ ለተወለደው ወንድ ልጅም ስም ያወጣችውም እሷው ነች። ታናሽ ወንድሜ የተወለደው ጣሊያን ሊገባ ስለ ነበረና በተወለደ በአስራ አምስት ቀን ሠፈራቸውን ትተው ስለ ተሰደዱ ስሙን "አሸብር" አለችው፡፡

በዚያን ጊዜ አባቴ አቶ በለጠ ሙያው ግብርና ሲሆን በተጨማሪም ይነግድ ነበር። ከሚኛ አለፍ ብሎ ካሉት ቆላ አካባቢዎች የሚኖሩት ሴቶች ወደ ደደር የሚያልፉት በማኛ በኩል ነው። እነኚህ ሴቶች ቡና በነጠላ ጫፍ ቋጥረው

ይዘው በዚያ ሲያልፉ ከእነኚህ ሴቶች ቡና ይገዛና አጠራቅሞ ወደ ከተማ ወስዶ ለአነ ከዋኝ ያኒ ይሸጣል። አባቴ በዚህ ሥራው እንድትረዳው ወጣትዋን አጸደን አለተምሯት ነበር። ቡና ከመግዛት ሌላ ወደ ቤታቸው ለሚመለሱትና ለመንደሩ ሴቶች ለመብራት (ላምባዲና) ጋዝም ትሸጥ ነበር።

ድክ ድክ በምልበት ጊዜ ከአባዬ ጋር እንደምውል ነግረውኛል። አንድ ቀን በከር አሰራቸው የነበረው የለንዱቆችና በሮች መከፈቻ ቁልፎች፥ ጠፉባት። ብትፈልግ፡ ብትፈልግ፡ አጣቻው፤ ሲጎበኛት ከመጣው ከአጎቴ ከአሰፋው ጋርም ቢፈልጉ አጡት። እኔ አይቼ እንደሆን ቢጠይቁኝ አላየሁም እንዳልኳቸው ያወራሉ፡፡ ከቀናት በኋላ ጋዝ ይያዝበት ከነበረው ታኒካ ዉስጥ ተገኘ፡፡ ታኒካው ዉስጥ እኔ እንደከተትኩት ይነገራል። "ይሄ ከይሲ" ተባልሁ፡፡

በሁለቱም ወላጆቼ በኩል ያሉት አያቶቼ አብዛኛውን ዕድሜአቸውን ሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት ያሳልፉ እንጂ አመጣጣቸው' ከሸዋ ነው፡፡ በአባቴ በኩል አያቴ ወልደገብርኤል ከሸዋ ወደ ሐረር የመጡት ሐረርጌ ገንዘብ ከሜሬት ይታፈሳል ይባል ስለነበር ነጋዴ ለመሆን አለበው ላይሆን አይቀርም። የአባቴ እናት ሴት







አያቴ እመት አየለች ባንኟው የመጀመሪያ ባላቸውን በጣልያን ጦርነት ያጡ መበለት ነበሩ፡፡ አያቴ እመት አየለች ከመጀመሪያ ትዳራቸው ለገሠ ቸሩ የሚባል ልጅ ነበራቸው፡፡ በመቀጠልም ወልደ ገብርኤልን አግብተው፡ አስካለን፥ በለጠን (የእኔን አባት) እና አሰፋውን ወለዱ። አቶ ወልደ ገብርኤል በሞት ሲለዩአቸው አቶ ገብረ ሥላሴን አግብተው ሦስት ልጆች፡- ዘውዴን፥ ዘነበችንና ደሳለኝን ወለዱ፡፡

አንዳንድ ጊዜ "እኔ የመምሬ ወልደሰንበት የልጅ ልጅ ነኝ" እያልኩ የምኩራራባቸው የእናቴ አባት መምሬ ወልደ ሰንበት በወጣትነት ዕድሜአቸው የማርያምን ታቦት ከሁለት ጓደኞቻቸው ጋር ከሸዋ ተሸከመው ወደ ሐረርጌ መጡ፡፡ ወበራ አውራጃ ደደር አጠገብ ልዩ ስሟ ደሩ በምትባል ቦታ ቤተ ክርስትያን አሰርተው የደሩ ማርያምን አቋቁመው፥ የመጀመሪያው ቄሰ ገበዝ ሆኑ፡፡ ለዚህ ተላትፎአቸው መንዲላ በሚባል ቦታ አንድ ቀላድ ተሰጥቶአቸው ስለነበር ግብርናን ተጨማሪ መተዳደሪያ አደረጉት።

ደሩ ማርያም ከምንኖርበት ከሚኛ፥ 20 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ትገኛለች፡፡ አንድ ቀን ከእናቴ ጋር ደሩ ማርያም መሄዳችንን አስታውሳለሁ። በቅሎአችንን መንደር ተውንና ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄድን። የመጀመሪያዬ እንደ መሆኑ ሥርዓቱን አላውቅም ነበር፤ ስለዚህም እናቴ የምታደርገውን እየተከታተልኹ እግር በግር ለማከናወን እጥር ነበር፡፡

እንደ ደረስን በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር የውጨኛው በር ላይ እናቴ እንደ መንበርከክ አለችና የበሩን መቃን ላመች። መሳለሟ ነው። እኔም እንዲሁ አደረግኹ። ወደ ግቢው ዘልቃ ስትገባ ተከትያት ዘው ልል ስል "አይ አንተማ በዚያ በኩል ግባ" ብላ የወንዶችን መግቢያ ጠቁማኝ እርሷ በቀኝ በኩል ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ዋና ሕንፃ ገባች፣ ተለያየን፡፡

ስንለያይ ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ግራ ገባኝ። ሌሎች ወንዶች የሚያደርጉትን እያየሁ ማድረግ ጀመርሁ፡፡ እንደ ገባን ግድግዳው ላይ ትልቅ ሥዕል ተስቅሎ ማየቴን አስታውሳለሁ፡፡ ሰዎች ሲገቡ ሥዕሉ ሥር ደፍት

ይላሉ፤ እኔም እንደዚያው ማድረግ እንደነበረብኝ ተረዳሁ፤ የከርስትና እምልኮ የጀመርኩት እንዲህ ባለ ሁኔታ ነበር ቤተከርስቲያን መሄድ ያስተማረችኝ እናቴ ናት የምለው ለዚህ ነው።

ዕድሜዬ ትንሽ ከፍ ሲል ከእረኞች ጋር በመዋል እረኝነትን መለማመድ ጀመርኩ፡፡ ውሎ አድሮ እረኝነትን የልጅነት ሥራዬ አደረግኩት፡፡ ታናሽ ወንድሜ እሸብርም አብሮኝ ይውል ነበር፡፡

አንድ ቀን ማታ እንደ ልማዳችን እናታችን ወጥ የምትሰራበትን ምድጃ ከበን እሳት ስንሞቅ እናትና አባታችን የሚያወሩት ወሬ ትኩረታችንን ስቦት በዝምታ እናዳምጥ ነበር፡፡ እናታችን አባታችንን እንዲህ አለቻው፡-

"ዘመዳችን መምሬ በኩረ የፈታውራሪ ገሠሠ ቆለጭን ልጅ ማስተማር ጀምሮአል አሉ፤ መሊሆንና እሸብር እዚያ ሄደው ትምህርት ቢጀምሩ ጥሩ ነው " ፡፡

"ከብቶቹን ማን ሊጠብቅልሽ ነው"? አባታችን መለሰ ኮስተር ብሎ፡፡

እናታችን ተስፋ ሳትቆርጥ መወትወቷን ቀጠለች፡፡ በመጨረሻም ተላከቶላት እኔና እሸብር እንድንማር አባታችን ፈቀደ፡፡ ሁኔታዎች ተመቻችተውልን ከአቶ ተከለማርያም ልጆች ግርማና ሽፈራው፥ ያቶ ወርቅነህ ልጅ አሰፋ ጋር በድምሩ እምስት ሆነን በአገልግል ምሳችንን ይዘን ወደ ደሩ ጢቆ ወደ ፊታውራሪ ገሠሠ ቆለጭ ግቢ ከልጃቸው ተሰፋዬ ገሠሠ (ከዘመናት በኋላ ታዋቂ እርቲስት የሆነው) ጋር አብረን መማር ጀመርን።

መምህራችን የኔታ በኩረ ከተሰፋዬ ገሠሠ በተጨማሪ ሌሎች ተማሪዎችም ነበሯቸው። ስለኛ መምጣት ቀደም ብለው ሰምተው ስለነበር ተቀብለውን ነባር ተማሪዎች እስጠኚ ተመድበውልን ፊደል ቆጠራ ጀመርን፡፡ ለእኔ የተመደብልኝ ፊደል አስቆጣሪ ተስፋዬ ገሠሠ ነበር።

ቡበራና ላይ የተጻፈ የፊደል ገበታ ተሰጠኝ፡፡ የፊደል ገበታው ትንሽ ዘንግ ላይ ተንጠልጥሏል፤ ተሰፋዬ በግራ እጁ ዘንጓን በቀኝ እጁ ለመጠቆሚያ የሸንበቆ ስንጣቂ ዘንግ እስያዘና ቀኝ እጄን እኔ ቀኝ እጅ ላይ አድርጎ ፊደሎቹን እየጠቆምን፤





ሀ ሁ ሂ.. እያለ ፊደል ያስቆጥረኝ ጀመረ፡፡ ከሀ እስከ ፐ ደጋግመን ከቆጠርን በኋላ እጁን ከእኔ እጅ ላይ እነሳና ራሴ ፊደሎቹን እንድጠቁም አደረገኝ። ሁላችንም በየፊናችን ሀ ሁ ሂ . . . በዜማ እንቆጥር ነበር፡፡ ደጋግመን ፊደል ቆጠርን፤ እኛ እረፍ ስንል ተሰፋዬ ወደ የኔታ በኩረ እግር ሥር ሄዶ ቁጭ ብሎ ወንጌል ማንበብ ጀመረ። እርሱ የከፍተኛ ከፍል ተማሪ መሆኑ ነው።

ፊደልን ወደ ጎንም ወደ ታችም ቆጥረን ስንጨርስ አ ቡ ጊ ዳ መማር ጀመርን፡፡ አ ቡ ጊ ዳን ወደ ጎንና ወደ ታች ካወቅን በኋላ ፊደል ሐዋርያ ተሰጠን። (ከመጽሐፍ ቅዱስ ፲ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ ፲ በግዕዝ ነበር) ፊደለ ሐዋርያን መጀመርያ እያንዳንዷን ፊደል ቆጠርን፡፡ ማንበብ ስንችል ቀጥሎ ወደ ወንጌል እንገባለን፤ ወንጌሉንም መጀመሪያ ፊደሉቹን እንቆጥራለን፤ ከዚያም ማንበብ እንጀምራለን። ወንጌል ማንበብ ስንችል ዳዊት ይሰጠንና ማንቡብ እንጀምራለን፤ ከዚያም ወደ ዳዊት መድገሙ እንገባለን። ዳዊት መድገም ስንጀምር ውዳሴ ማርያም ለመድገም እንጀምራለን። የውዳሴ ማርያም ድግምት ትምህርት ማታ ማታ ነበር፡፡

ፊደለ ሐዋርያ ስንጀምር የግርማና ሽፈራው እባት አቶ ተከለማርያም ለፓርላማ ተመርጠው (ተሹመው) ከነቤተሰባቸው ወደ አዲስ አበባ ሄዱ፡፡ ወንጌል ማንበብ እንደ ጀመርሁ አዲስ አበባ ለሚገኘው ጓደኛዬ ግርማ ደብዳቤ ለመጻፍ ፈለግኩና የኔታን ስለ ደብዳቤ አጻጻፍ ጠየኳቸው። እርሳቸውም እንዲህ ብለህ ጻፍ አሉኝ፡-

"ይድረስ ለግርማ ተከለ ማርያም፤

የምድር ስፋቱን፥ የሰማይ ርቀቱን፣ ያህል እንደምን እለህ? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። ይላል መሊሆን በለጠ፡፡"

ይህቺን ደብዳቤ ጽፌ፥ በፖስታ መላክ ስለማላውቅ ወረቀትዋን በልዩ ዘዴ እጣጥፌ ስሙን ከውጭ ጽፌ ወደ አዲስ አበባ ከሚሄድ ሰው ጋር ላኩት። የተማርኩትን በስራ ላይ በማዋሌ ኩራት ተሰማኝ፡፡

ጥቂት ጊዜ ቆይቶ ትምህርት ቤታችን ተግዳሮት ገጠመው፡፡ ግርማና ሽፈራው ከአባታቸው ጋር ወደ አዲስ አበባ ከሄዱ በኋላ አሰፋ ወርቅነህ አልማርም ብሎ ወጣ። ወንድሜ አሸብር ፊደል አልገባ ሰላለው ወደ እረኝነቱ ተመለሰ። እኔና ተስፋዬ ብቻ ቀረን። እኔም ዳዊት መድገም እንደ ጀመርኩ ትምህርቴን አቆምኩና ወደ እረኝነቴ ተመለስሁ። አሸብር ግን ወደ መንዲሳ ሄዶ እናዬ (የእናታችን እናት እያታችን) ጋር እየኖረ እዚያ የቄስ ትምህርት ቤት ገባ። በዚያ ጎበዝ ተማሪ እንደሆነ እንሰማ ነበር።

እረኛ ብሆንም እንኳን ንባብ በመቻሌ ምክንያት በመንደራችን ለሁለት ጉዳዮች ተፈላጊ ሰው ሆንኩ፡፡ አንደኛ፡- ሰው ሁሉ ደብዳቤ ሲላክለት ወይም ከፍርድ ቤት መጥሪያ ሲደርሰው ማንበብ የምችል እኔ ብቻ በመሆኔ እንዳነብላቸው ይፈልጉኝ ጀመር፡፡ ሁለተኛው ከመፈለግ ሰሜቱ ባለፈ ክብር እንዲሰማኝ የሚያደርገኝ ጉዳይ ዉዳሴ ማርያም በመድገም ችሎታዬ ምክንያት በመንደራችን ለሚደረግ ማንኛውም ዝክር መፈለጌ ነበር፡፡ እናቴ ለማርያም፥ ለገብርኤል፥ ለሚካኤል ትዘክር ነበር። ጸዲቁን ውዳሴ ማርያም ደግሜ የምቆርስ እኔ ነበርኩ። በተለይ የገብርኤል ዝክር ቀን በተለይ ታህሳስ 19 ቀን በመንደሩ ብዙ ቤቶች ይዘከራሉ። ድፎ ዳቦ ይቀርባል፤ ጠላም ይጠመቃል፤ ሰው ሁሉ በተሰበሰበበት ለመባረክና ለመድገም ሰቆም ሁሉ ሰው ይቆማል፡፡ ክብር እየተሰማኝ "በሰመአብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈሰ ቅዱሰ፣ አሃዱ አምላክ . . ." ብዬ ድፎ ዳቦውን በቢለዋ እቆርሰዋለሁ። ከዚያም ለሰው ሁሉ ይታደላል፡፡ ምሲጋና ለችሎታዬ ይድረሰውና በመንደሩ የተከበርኩና ተፈላጊ አደረገኝ። ብዙዎች "በእያቱ በመምሬ ወልደሰንበት ሊወጣ ነው" ሊሉ እሰማቸው ነበር።

ይህ ተፈላጊነትና ክብር ያሰገኘልኝን ትምህርት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለማድረስ እየተመኘሁ የእረኝነት ስራዬን ቀጠልኩ፡፡





## ሲቀጥል

ከመንደራችን በቅርብ ርቀት በምትገኘው ደደር ከተማ (ከተማ እንበላትና) ትገኛለች፡፡ ከተማዋ እስኳላ (ዘመናዊ) ትምህርት ቤትም ተከፍቶላት ነበር። ብዙ ሰዎች ወደ ከተማዋ በሚመላለሱበት መንገድ አጠገብ ነበር ሁልጊዜ ከብቶቼን እሰማርቼ የእረኝነት ስራዬን የማከናውነው፡፡

ከተመላላሾቹ ውስጥ ልዩ ትኩረቴን የላበው ከተማ ገሠሠ ነበር፡፡ ከተማ ገሠሠ እኛ ከምኖርበት ከሚኛ እልፋ የምትገኝ መንደር ውስጥ ነዋሪ የሆነ ልጅ ነው። በየዕለቱ ከመንደሩ ከ17 እስከ 20 ኪሎ ሜትር ርቀት በመጓዝ ደደር ውስጥ የሚገኝ አበራ ግዛው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይማር ነበር፡፡ ከተማ ገሠሠ ከሌሎቹ መንገደኞች በተለየ ሁኔታ ከእኔ ጋር ጊዜ ማሣለፍ ይወድ ነበር፤ በተለይ ከትምህርት ቤት መልሰ እኔ ጋ እረፍ ይልና ሰለ ትምህርት ቤቱ ያጫውተኛል። እፌን ከፍቼ የሚነግረኝን የትምህርት ቤት ትዕይንት በዓይነ ህሊናዬ እየቃኘሁ እዳምጠዋለሁ፡፡ እረኝነቴን ትቼ እብሬው ተመላልሼ እንድማር ይጎተጉተኝ ነበር፡፡ የከተማ ገሠሠ ገለፃና ጉትጎታ ከዕለት ወደ ዕለት ውሰጤ እየሰረፀ መጣ። ተፈላጊና የምከበር ሰው ሆኜ የመቀጠል ፍላጎቴ ተነሣሣ፡፡ ትምህርቴን የተሻለ ደረጃ የማድረሰ ህልሜ ተቀሰቀሰ፡፡ እኔም እንደ እርሱ ደደር ሄጄ ተማሪ መሆን ፈለግሁኝ፡፡

አንድ ቀን ማታ ለእናቴ "ደደር ከተማ ት/ቤት ልገባ እፈልጋለሁ፤ እዚያ የፈረንጅ ቋንቋም እማራለሁ" እልኳት። እናቴ በሃላቤ ደሰ ተሰኝች ደገፈችኝም ፤ ለአባቴ እንደምትነግረው ቃል ገባችልኝ፡፡ ለአባቴ ሰትነግረው እንደ ቀድሞው ሁሉ "እርሱ ተማሪ ቤት ከገባ ከብቶቹን ማን ሊጠብቅልሽ ነው?" አላት፡፡ እናቴም ራሷን ለመልሰ አዘጋጅታ ሰለነበር "ከብቶቹን ዓለሚ ትጠብቅ" አለቺው (ዓለሚ እናታችንን በቤት ውስጥ ሥራ የምትረዳት ነበረች)። እናቴ በማንኛውም ሁኔታ እኔ እንዳልማር እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ቀድማ በመዘጋጀት በጥበቧ እሣለፈችኝ፡፡

ትልቅ ድል! በአስራ ሦስት አመቴ ደደር ትምህርት ቤት በ1938 ዓ.ም ገባሁ! ደደር ከሚኛ 12 ኪሎ ሜትር ያህል ይርቃል፤ እኔም እንደ ከተማ ገሠሠ ከሚኛ ደደር እየተመላለስሁ መማር ጀመርሁ!። ጠዋት ፀሐይ ስትወጣ ቁርሴን በልቼ ከቤት አወጣለሁ፤ ትምህርት ቤት የከተማው ልጆች ሁሉ ከፍል ከገቡ በኋላ አደርሳለሁ፡፡ ትምህርቴን ስማር አውልና በምሳ ጊዜ በኪሴ ይዤ የመጣሁትን ቆሎ በልቼ ከወቢ ተራራ የሚፈሰውን የምንጭ ውኃ አጠጣለሁ፡፡ የምሄድበት ቦታ ስለሌለኝ ባሕር ዛፎች ጥላ ሥር ተቀምጬ አጠናለሁ፡፡ ባሕር ዛፉ ውስጥ ብቻዬን አልሆንም፣ እንደ እኔና ከተማ ሌሎችም እየተመላለሱ የሚማሩ ልጆች ስለነበሩ ከእነርሱ ጋር የጥናትና የጨዋታ ጊዜ ይኖረኝ ነበር፡፡

እንዲህ ባለ ሁኔታ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን መማር ቀጠልኩ፡፡ ከሁለት አመት በኋላ ግን ከቤት ብቻዬን መውጣቱ አቆመ፡፡ አሸብርም ከመንዲሳ መጥቶ ከእኔ ጋር ደደር እየተመላለስን መማር ጀመርን። ደስታዬ እጥፍ ሆነ፡፡ እኔና አሸብር ጠዋት ፀሐይ ስትወጣ የወጣን ማታ ፀሐይ ስትገባ ወደ ቤት እንመለሳለን፡፡ ጊዜን የምንለካበት ሰዓት አልነበረንም፡፡ ጊዜውን ስይተን የምናውቀው ጥላችንን በመለካት ነበር፡፡ ጧት የወጣን ማታ ስለምንገባ፣ ምሣ አግኝተን ስለማንመገብ ማታ የሚቀርብልን ምግብ እንዴት ጣፍጦን እንበላ እንደ ነበር ትዝ ይለኛል፡፡

***

በመካከሉ በ1940 ዓ.ም አባቴ ሐረርቲ የሚባል አገር መሬት ገዛና ቤተሰቦቻችን በሙሉ ወደ ሐረርቲ ተዘዋወሩ፡፡ እኔና አሸብር ከማን ጋር እየኖርን ትምህርታችንን መቀጠል እንደምንችል ስጊዜው መልስ ያላገኘ ጥያቄ ሆነ፡፡ ከስንት ሃሳብና መላ ፍለጋ በኋላ የአባቴን መሬት የሚያርሰው ያአቶ ቶላ ባለቤት እመት አስካለ ምግብ እንድታበስልልን ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡ አስካለ ለእኛ ምግብ መስራቱ እንዳይሰለቻት ከትምህርታችን ጎን ለጎን ውኃ ከወንዝ በመቅዳት፣ እህል በመፈተግና እንጨት በመልቀም እናግዛት ነበር፡፡ ሐረርቲ በየሳምንቱ ስለምንሄድ እንጨት በእህያ ጭነን እናመጣላት ነበር፡፡ እንጨት ስመልቀም ጊዜ ሲያጥረን የማሽላ ቀራ ይዘን እንመለሳለን፡፡ በተለያየ ምክንያት በጊዜ ጉዞአችንን





ስለማንጀምር መንገድ እየመሸብን ከጅብ ጋር እንፋጠማለን፡፡

አንድ ቀን እንደተለመደው መንገድ ላይ መሸብን፤ መብራት ስለ ሌለን ጅብ ከየት አቅጣጫ እንደሚመጣ መለየት እንኳን አንችልም ነበር፡፡ ስለዚህ አንደኛችን ከፊት አንዳችን ከኋላ ሆነን አህያዋን ከመሐል አድርገን እንጓዛለን፡፡ በዚያ ጭለማ ውስጥ ከአሁን አሁን ጅብ መጥቶ አህያዋን ነጠቀን በሚል ፍርሃት ተሸብበን ስንጓዝ ድንገት አህያዋ ቆመችብን፤ ልባችን አብሮ ቆመ፡፡ ለምን እንደቆመች ለመረዳት በመፈለግ ብድቅድቁ ጭለማ ውስጥ ወደ ግራ ወደ ቀኝ ወደ ኋላ ስማየት ሞከርን፣ ምንም አይታየንም ጨነቀን፡፡

ያው ተፈጥሮ እንዳደላት፣ በደመ ነፍሷ ጠላቷ ጅብ በአካባቢዋ እንዳለ ተሰማት መሰለኝ አህያዋ በተገተረችበት ሆዷ መንጪረር (መጮህ) ሲጀምር በአካባቢያችን ጅብ መኖሩን ተረዳን፡፡ የእኛ ሆድ እንደ አህያዋ አልጮኸም እንጂ ፍርሃታችን ከአህያዋ ያልተናነሰ ነበር፡፡

ግራና ቀኛችንን በፍርሃት ፍጥነት ስንቃኝ በአንድ አቅጣጫ ጅቡ ጢሻ እየጣሰ ወደ እኛ ሲመጣ ኮሽኮሽታው ተሰማን፡፡ እንደ ምንም ወኔያችንን አሰባስበን ፍርሃት በተላቀለበት በማስፈራራት ድምጽ ስንጮህበት ከአካባቢው ሸሽቶ ሄደልን፡፡ አህያዋም ፍርሃቷ ለቋት መራመድ ጀመረችልን፤ ቤታችን በሰላም ደረስን፡፡ እንዲህ እያልን ነበር በሰቀቀንና ፍርሃት ቤታችን የምንደርሰው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የሚከታተሉን ጅቦች ቁጥራቸው በዝቶ ከፍርሃት ፉከራችን በላይ ሲሆኑብን እቅማችንን ገምተን ወደ ሰው ቤት ተጠግተን እናድር ነበር፡፡

በየሳምንቱ ቅዳሜ ሐረርቲ ስንሄድ ከምናደርጋቸው ነገሮች ትዝ የሚለኝ የራሣችንና የወላጆቻችንን ልብስ ይዘን ወንዝ በመሄድ የማጠባችን ነገር ነው፡፡ አድርቀን ወደ ቤት ስንመለስ ደግሞ እንተኩሣለን፡፡ ካውያውን ማጋል የሙተኮስ ስራችንን ከባድ ያደርግብናል፡፡ የዛን ጊዜ ካውያ ውስጡ እሳትና ማቀጣጣያ ከሰል ወይንም ረግፎ የደረቀ የባሕር ዛፍ ፍሬ ተጨምሮበት ነበር የሚግለው። ከሰል ማግኘት ስለማይቻል የበቆሎ ቆረቆንዳ ጨምረን ማጋል ይጠበቅብን ነበር።

እንዲህ ባለ ሁኔታ ሁለት አመታትን ከገፋን በኋላ ከፊት ለፊታችን ከባድ ችግር ተጋረጠብን። ምግብ የምታበስልልን የአሰካለ ባለቤት እቶ ቶላ ታሞ ሞተ። የእኔና የአሽብር ትምህርት እንደገና ፈተና ገጠመው። ትምህርታችንን ማቆም አልፈለግንም። ምን እናድርግ? ጭንቅ ሆነብን። በመጨረሻም መለያየት ግድ ሆነ። አሽብር ደደር ወዳለችውና ፖሊስ ባል ወዳላት የአከስታችን ልጅ አባዬ የሺ ጋር ተጠግቶ ከወንድሟ ልጅ ከፍስሐ ጋር ወደ ትምህርት ቤት በመሄድ ትምህርቱን ቀጠለ። እኔ እዚያው ሚኛ አከስቴ አባዬ ዘነበችና ጋሼ አሸቴ ጋር ተጠጋሁ።

ጥቂት ጊዜ አብሬያቸው እንደ ኖርኩ ሌላ ችግር ተከሰተ። ባልና ሚስት ተፋቱና አባዬ ዘነበች ከቤት ወጣች። እኔስ ምን ላድርግ? ከአከስቴ ጋር ልውጣ? ምን መወሰን እንዳለብኝ ተቸገርሁ፤ እንዲሁ እያቅማማሁ ከጋሽ አሸቴ ጋር መኖር ቀጠልኹ። ሁለት ወንዶች ብቻችንን ራሳችንን መግበን መኖር አስቸጋሪ ሆነብን። ጎረቤቶቻችን ምግብ ይሰሩልን ነበር። ወጥ ሰርተው፣ እንጀራ ጋግረው ቤት ያመጡልናል፤ እኔ ከት/ቤት ስመለስ እነርሱ ሰርተው ያመጡትን ወጥ አሙቄ እንጀራ ከሌማት ውስጥ አውጥቼ በማቅረብ አብረን እንበላ ነበር። ትምህቴን ሳላቋርጥ መቀጠል መቻሌ አስደስቶኝ እኖር ነበር። ጋሼ አሼቴ ግን አልፎ አልፎ "አንተ ልጅ ወደ ዘመዶችህ ብትሄድ ይሻልሃል" ይለኝ ነበር።

እንዲህ እየኖርን እያለ ጋሼ አሼቴ ሌላ ሚስት አገባ፤ አሁንም ቢሆን ከቤት ለመውጣትም ሆነ እዚያ ለመኖር ከሁለት አንዱን መወሰን ነበረብኝ። አንድ ቀን በቅርብ የሚኖር አጎቴ ጋሼ አሰፋው "እንግዲህ በቃህ፣ ውጣ" ሲል መከረኝ። ወጣሁና ማደሪያዬን አጎቴ ጋሼ ደሳለኝ ቤት አደረግሁ። ምግቤን አዛም አዛም እያልኩ መብላት ጀመርኹ፤ አንዴ አያቴ ቤት፣ አንዳንዴ ደግሞ አጎቶቼ ቤት በመሄድ እመገብ ነበር። አዛም አዛም እያልኩ መመገቤን ያልወደደው አጎቴ አሰፋው አንድ ቀን እራት እየበላን እያለ ሚስቱን እትዬ ደብሬን "መሊሆን እዚያም እዚያም ከሚል እዚሁ ብቻ ይብላ" አላት። ንግግሩን ስሰማ ለምግብ ምንከራተቴ ሊያቆም መሆኑ ተሰምቶኝ ደስ አለኝ። እትዬ ደብሬ ብዙም ሳታቅማማ "እኔ





አልችልም" ስትለው ደስታዬ ላይ ውሃ ጨመረችበት። አጎቴ አሰፋው ወደ እኔ ዞር ብሎ "እንግዲያው እናዬ ዘንድ ብላ" አለኝ። ቀስ ብዬ "እሺ" አልኩ። አያቴ፥ እናዬ ዘንድ እየበላሁ ጋሼ ደሳለኝ ቤት እያደርሁ በሳምንቱ መጨረሻ ደግሞ ወደ ሐሪርቲ እየሄድኩ ትምህርቴን ቀጠልሁ።

አንድ እሁድ እራሴን በጣም አመመኝ። ራሰ ምታቱ አላንቀሣቅስ ስላለኝ ሕመሙ እስኪለቀኝ ድረስ ከትምህርት ቤት ቀርቼ ቤት ተኛሁ። በሚቀጥለው ሳምንት አባቴ ትምህርት ቤቴ ሄዶ የቀረሁበትን ምክንያት ሲያስረዳቸው ከከተማው ክሊኒክ መድሃኒት ይዞ እንዲሄድ ስለ መከሩት መድሃኒት ይዞልኝ መጣ። "ሐኪም ታደሰ ይህን እንድትውጥ ብሎሃል" ብሎ ነጫጭ ነገሮች ሰጠኝ። ኪኒኖቹን ሳይ ገረመኝ። "የታመመው እራሴ ነው እንጂ ሆዴ አይደለም፤ እራሴን የምቀባው መድኃኒት መስጠት ሲገባው እነኚህን ዋጥ ማለቱ ምን ማለቱ ነው?" ብዬ ራሴን ጠየኩ ፤ ራሴን ቅቤ ቀብቼ ከሕመሜ የምገላገልበት ነገር ባላገኝም እንደ ተባልኩት ኪኒኖቹን ዋጥኩ፤ አላዳነኝም። እናቴ እናቴ ላይ ቅቤ አድርጋ ሻሽ ስታስርልኝ የተሻለኝ ይመስለኝ ነበር።

ሕመሜ እየፀና የመዳኔ ነገር እየራቀ ሲሄድ፥ ያድነዋል የተባለ ነገር ሁሉ ይሞከርልኝ ጀመር። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ በሐረር እስላም ኦሮሞዎች ልማድ ወዳጃ የሚባለው ነው። በዕለቱ ቤታችን ለወዳጃ የተሰበሰቡት ወንዶች ጫት ይቅሙና፤ ሆጃ ይምት ነበር።

ወደ አኩለ ሌሊት ላይ እኔ ጥብቆዬን አውልቄ መሐከላቸው እንድቀመጥ ተደረገ። ዝየራቸውን (መዝሙራቸውን) እየተቀባበሉ እየዘመሩ ሞቅ ሲላቸው አፋቸው ላይ ውኃ ጎንጨት ያደርጉና በጊዜው ብዙ የማይገቡኝን ብዙ ቃላትና ሐረጋት ደጋግመው በዜማ እያሉ (እየደገሙ) የተጠናወተኝን በሽታ (መንፈስ) ለማስወገድ ከዚያም ከዚህም አንትፍ! አንትፍ! ይሉ ነበር፤ "መንፈሱንም" ያዙት ነበር። ምንም የሚሻለኝ ነገር ግን አልነበረም። እንዲያውም ያለማቋረጥ በግራና በቀኝ በዝየራና በቱፍታ ሲዋከቡኝ የበለጠውን እናቴ ተናጋ፤ ሳስበው አሰማበዴ ያስገርመኛል።

ሌላ ሁለት ላምንት ታምሜ ተኛሁ፡፡ ከሕመሙ የባሰ ያስቸገረኝ ቅዠት ነበር። ልሞት ይሆን? በጣም ተጨነኩ። በግብረ ገብ ትምህርት ሰው ሲሞት ወደ ገነት ወይም ወደ ገሃነም እንደሚሄድ ተምሬአለሁ፡፡ የት እንደምሄድ የሚወስነው በምድር ላይ የሰራሁት ስራ ነው፡፡ ሥራዬ ተመዝኖ መልካሙ ከመዘነ ገነት፣ ከፋት ካመዘነ ገሐነም እገባለሁ። ሥራዬን ሳሰበው የትኛው እንደሚያመዝን አላወቅሁም፤ በጣም ፈራሁ። ከራስ ምታቱ ይልቅ ያሰቃየኝ ይህ ሃሳብ ነበር። በጣም ተጨነኩ ... "የአሁኑን ብቻ ልዳን እንጂ ጥሩ ሰው እሆናለሁ" ስል ቃል ገባሁ። የምርም ጥሩ ሰው ለመሆንም ታላቅ ፍላጎት አደረብኝ።

ወላጆቼ ብዙ ጥረውልኛልና ከተሞከሩልኝ ሁሉ የትኛው እንዳዳነኝ ባላውቅም፡ ተሻለኝ። ነገር ግን ወደ ትምህርት አልተመለስሁም። ራሴን ያመመኝ ከትምህርት ብዛት እንደ ሆነ የተነገረኝን ሳላምን አልቀረሁም፤ ስለዚህ ፊቴን ወደ እርሻ አዞርኩና አባቴን መሬት እንዲሰጠኝ ጠይቅሁት፡፡ አንድ ጫካ መሬት ሰጠኝ፤ ደበ ጠራሁና ቦታውን አለመንጥሬ ለጫት ተከላ አዘጋጀሁት፤ ተከልኩበትም። ያም የጫት ቦታ እስከ ደርግ ዘመን ድረስ "የመሊሆን ጫት" እየተባለ ይጠራ ነበር።

ትምህርቴን አቋርጬ በግብርና ተሠማርቼ መኖር ጀመርኩ፡፡ በዚህ ሁኔታ እያለሁ አቶ ብሥራት የሚባል የአውራጃው ፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ሹም የነበረው ወደ አፍደም ተዛውሮ ስለነበር ለጉብኝት መጣ። ከተዛወረበት ቦታ ሊጠይቀን ሲመጣ ትምህርቴን አቁሜ ግብርና እንደ ቀጠልሁ አየ። ባለኝ እውቀት ፍርድ ቤት ልሠራ እንድምችል ለላመነ አውራጃው ፍርድ ቤት ደጅ እንድጠና አደረገኝ። ደጅ እየጠናሁ ሳለ ደብዳቤ መጻፍ እሰራ ነበር፡፡

የባላገር ሰዎች ክስ መመስረት ፈልገው ወደ ፍርድ ቤት ይመጡና ጉዳያቸውን ያሣውቃሉ፡፡ ቀላል ክስ ከሆነ ደብዳቤውን እኔ አርቅቄ እጽፋለሁ፡፡ ጉዳዩ ከበድ ያለ ከሆነ ግን የከሰ ደብዳቤውን መደበኛ ማመልከቻ ደብዳቤውን አለቃዬ





ያረቅና፤ እኔ በሁለት ኮፒ እገለብጠዋለሁ፡፡ ባለ ጉዳዩ ሁለት ሽልንጎች (50 ሳንቲም) ይከፍለኛል፤ እንዱን ማመልከቻውን ላረቀቀው አለቃዬ እሰጠውና እንዱን ወደ ኪሴ እሰገባለሁ፡፡ እንደዚህም ሆኖ የምትከፈለኝን አንድ ሽልንግ እጠራቅሜ ቁምጣ ሱሪ ገዝቼ ሽክ ማለት ችዬ ነበር።

ደደር አውራጃ ፍርድ ቤት አጠገብ ያውራጃው ግምጃ ቤት ነበር። ከተማ ገሠሠ በዚያ ግምጃ ቤት ተቀጥሮ ይሠራ ነበር። ከተማ ደደር ትምህርት ቤት እንድገባ የገፋፋኝ ጓደኛዬ መሆኑን ያስታውሷል፡፡ ከከተማ ጋር ብዙ ጊዜ አብረን እናሳልፍ ነበር፡፡ አንድ ቀን እንደ ተለመደው በምሣ ጊዜ ተገናኝተን በእረፍት ሰዓታችን ምን እንደ ምናደርግ ስንወያይ "ለምን ሚሽን ትምህርት ቤት የሚማሩትን ጓደኞቻችንን አናይም" የሚል ሃሳብ ተነሣ፡፡ በጉዳዩ ተሰማምተን ጓደኞቻችንን ለማየት ወደ ሚሽን ትምህርት ቤት ሄድን። ጓደኞቻችን ሚሽን ትምህርት ቤት ከገቡ አንድ ወር ሆኗቸው ነበር። እዚያ ስንደርስም ትምህርት ገበታ ላይ ነበሩ።

የምታስተምራቸው አንዲት ፈረንጅ ነበረች፤ በሩ ክፍት ስለነበረ ውጭ ስንንጎራደድ መምህርቷ አየችን፤ ማንነታችንን ስለነገሯት ፈረንጂቱ ወጣ አለችና' እንድንገባ ጋበዘችን፡፡ ከሰውነቷ ምልከት ግቡ እንዳለቺን ስለተረዳን ገብተን ተቀመጥን። በመቀጠል አንድ ነገር ብላ ወደ ፊታችን ትንሽ ወረቀት ገፋ አደረገች፡፡ እኔና ከተማ ምን እንዳለችን ስላልገባን አይናችን ፈጠጠ "ስማችሁን ጻፉ ነው የምትላችሁ" አሉን ጓደኞቻችን፡፡ ወረቀቱን ተቀብዬ ስሜን እየጻፍኩ በእወንታዊ ቅናት ልቤ ተቃጠለ "ከምኔው እንደሷ መናገር ቻሉ? . . . ምነው እኔም እንደነሱ መናገር በቻልኩ" የሚል ቅናት አደረብኝ። በዚያው ቅጽበት በልቤ የእነርሱን ያህል እንኳ እንግሊዝኛ እንድችል ለአንድ ወር ያህል ትምህርቴን ልቀጥል ወሰንሁ። ለሕይወቴ ታላቅ እመርታ ያደረገው ክስተት ተለከሰ፡፡

## ደደር ሚስዮን ትምህርት ቤት

የሜኖናይት ሚሲዮን በደደር ትምህርት ቤት ሲከፍቱ ከደደር መንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንዳትቀበል አስተማሪዋን ሚልድረድ ሂስታንድን ቃል አስገብተዋት ነበር። በደደር ትምህርት ቤት ከፍተኛ ክፍል የነበርነው ተማሪዎች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ለመግባት የመግቢያ ፈተና ይመጣላችኋል ተብለን ብዙ ጠብቀናል፡፡ ፈተናው ግን አልመጣም። ተማሪዎቹ በሙሉ መበታተን ጀምረናል፡፡ እኔ በሕመም ምክንያት ትምህርቴን አቋርጬአለሁ። ጥቂቶቹ ወደ ሐረርና፣ ድሬዳዋ ሄደዋል። የቀሩት ተማሪዎች አንድ ቀን ተሰብስበው ወደ ሚልድረድ በመሄድ አስተምራ የሁለተኛ ደረጃ ፈተናን እንድታስፈትናቸው ጠየቋት፡፡ "አልችልም፥ ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ላልቀበል ቃል ገብቻለሁ" አለቻቸው።

ተማሪዎቹ ምን ብናደርግ ይሻላል? ብለው ተመካከሩ፤ ከደደር ትምህርት ቤት እንሰናበትና የስንብት ደብዳቤአችንን እናቅርብላት በሚል ሃሳብ ተስማሙ። ወደ አጋፋሪ ዘውዴ ሄደው፡- "ጓደኞቻችን ወደ ሐረር፣ ድሬዳዋ ሄደዋል፤ እኛም ወደዚያው ሄደን ለሁለተኛ ደረጃ የሚያበቃ ትምህርት ለመከታተል እንፈልጋለንና አሰናብቱን፣ የስንብት ወረቀትም ይሰጡን" ሲሉ ጠየቋቸው።

አጋፋሪም መልካም ብለው ለእያንዳንዳቸው የስንብት ወረቀት ሰጥተው ሸኙዋቸው። ተማሪዎቹ ግን የስንብት ወረቀታቸውን ይዘው ወደ ሚልድረድ በመሄድ ከደደር ትምህር ቤት መሰናበታቸውን በማስረጽ እንድትቀበላቸው ጠየቋት፡፡ ሚልድረድ ተቀበለቻቸውና ደደር ሚሽን ትምህር ቤት መማር ቀጠሉ፤ ትንሽ ቆይቼ እኔም ተቀላቀልኳቸው።

አጋፋሪ ዘውዴ ለሐረርጌ ት/ቤቶች ጽሕፈት ቤት ባቀረቡት ክስ ምክንያት ላይሆን አይቀርም አለቆች አንድ ቀን በትምህርት ላይ እያለን በድንገት ወደ ሚሽን ትምህር ቤት መጡ፡፡ ትምህርት ቤቷ ሁለት ክፍሎች አሉዋት፡፡ እያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ሁለት ወይም ሦስት የክፍል ደረጃዎች አሉ፡፡ መምህራት ሚልድረድ





ሂስታንድና አንድ ረዳትዋ ብቻ ነበሩ። ሚልድረድ ሂስታንድ ሶስቱን ክፍሎች ታስተምራለች። ለአንዱ ደረጃ የምታስረዳውን አስረድታ የክፍል ውስጥ ስራ ትሰጥና ሌላውን ደረጃ በተመሣሣይ ሁኔታ ማስተማር ትቀጥላለች፡፡ አንደኛው ደረጃ ገለፃ ሲደረግለት ሌላው የክፍል ሥራ ይሠራል፡፡ እንዲህ ባለሁኔታ እያስተማረች እያለ ነበር ሁለት የሐረርጌ ትምህር ቤቶች ሹማምንትና አጋፋሪ ዘውዴ የመጡት።

መምጣታቸውን እያወቅን የአለቱን ከንውን ቀጥለናል፡፡ "ምን ፈልገው ነው?" "ትምህርታችንን ሊያስቆሙን ይሆን?" የሚለው ስጋት ግን ውስጣችንን በጭንቀት አመሰው፡፡ ዐይናችን ደብተራችን ላይ ቢያፈጥም ልባችንና ጆሮአችን ግን እነሱ ጋር ነበር፡፡ በተለይ እኔ ለንት ተግዳሮት አልፌ ያገኘሁት ዕድል በምንም ምክንያት እንዲሰናከልብኝ አልፈልግም ነበርና ጭንቀቱ እየለብኝ፡፡

ሹማምንቱ አስተማሪዋ የምታደርገውን በጥሞና ሲመለከቱ አጋፋሪ ዘውዴ ወደ ጆሮአቸው ጠጋ በማለት፣ ወደ እኛ እያመለከቱ "እነኚህ ናቸው" ሲሉ ለማናቸው። ከሚልድረድ ሂስታንድ ጋር መነጋገር ቀጠሉ፤ ሚልድረድ ሂስታንድ፣ ወደ እኛ እያሳየቻቸው፡-

"እነዚህ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ፈተና እንዲፈተኑ እፈልጋለሁ፣ ምን ማድረግ አለብኝ?" አለቻቸው። "ሥርዓተ ትምህርቱን (ካሪኩለሙን) ተከትለሽ ካስተማርሻቸው ማስፈተን ይቻላል" በማለት አቶ ሰይፉ ዘለቀ መለሰላት። ካሪኩለሙንም አሳያት፤ አገላብጣ ካየች በኋላ፡-

"ይህን ካሪኩለም የት ላገኝ እችላለሁ?" በማለት ጠየቀችው። "እኛ እንልከልሻለን ነገር ግን ነገ ወደ መንግስት ትምህርት ቢሮ ብቅ በይና እንነጋገር"

በማለት ለቀጣዩ ቀን ቀጠሮ ተለዋውጠው ተለያዩ፡፡ ሚልድረድ ከለብሰባው ይዛው የምትመጣውን ዜና በሰቀቀን መጠባበቅ ቀጠልን፡፡ "ትምህርታችንን አቁሙ" ብንባልስ? የሚለው ሃሳብ ሽው ሲልብኝ ስጋት ይለቅብኝ ነበር፡፡

ከሰዓት በሁዋላ ከፍል ስትመጣ ሌላ የእንግሊዝኛና የቁጥር መማሪያ መጻሕፍት ይዛ መጣችና አደሰችን፤ ማስተማሯን ቀጠለች፡፡ ትምህርቴን መቀጠል በመቻሌ እፎይታ ተሰማኝ፡፡ የውይይታቸውን ዝርዝር ምን እንደሆነ ባትነግረንም ትምህርት መቀጠል መቻላችን አስደሰተኝ፡፡

ትምህርታችንን እንቀጥል እንጂ ሹማምንቱ በገቡት ቃል መሠረት ካሪኩለሙን አልላኩላትም፡፡ ዶክተር ሽሌባከ የሚባል የሚሲዮኑ የሕክምና ዶክተር አዲስ አበባ ስሥራ ሄዶ በነበረብት ጊዜ ከትምህርት ሚኒስቴር ካሪኩለሙን ይዞላት መጣ። በጣም ደስ አላት። በካሪኩለሙ መሠረት ግንቦት ወር ላይ ለሚደረገው ፈተና ዝግጅት ማስተማሯን ቀጠለች፡፡ እኛም ይበልጥ ተነቃቅተንና ተደስተን መማራችንን ቀጠልን።

ድሬዳዋ በመማር ሳይ ካሉት ጓደኞቻችን ፈተናው ግንቦት 27 ቀን 1944 ዓ.ም እንደሚሰጥ ሰማን። ፈተናው እንዲመጣልን ወደ ትምህርት ሚኒስቴርና ወደ ሐረርም ደብዳቤ እንድትጽፍ ለሚልድረድ አሳሰብናት፡፡ እርሷም ደብዳቤ ወደ ትምህር ቤት ሚኒስቴርና ወደ ሚመስከታቸው ሁሉ ጻፈች። የፈተናውን መምጣት በጉጉት እየጠበቅን ትምህርታችንን በትጋት መማር ቀጠልን፡፡ ሁላችንም በጉጉት የምንጠብቀው የደብዳቤው መልስ ግን ዘገየብን፡፡ እልፎ እልፎ የስጋት ነፋስ በልባችን ሳይ ሽው ከማስቱ በስተቀር በደስታ ለፈተና መዘጋጀታችንን ቀጥስናል።

ወደ ግንቦት አጋማሽ በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት ት/ቤቶች ሥራ አስኪያጅ የተፈረመ ደብዳቤ ደረሳት። ደብዳቤው ባጭሩ "ያንቺ ተማሪዎች በመንግሥት ትምህርት ቤት ካሉት ከስድስተኛ ከፍል የማይበልጡ ስለሆኑ ፈተና አይላከልሽም" የሚል ነበር፡፡ የሁላችንም ልብ ፈሰሰ፣ ትጋታችን መሸርሸር ጀመረ፤ ትምርቱን ቸል ቸል አልነው፤ ጥቂቶች ቀረት ቀረት ማለት ጀመርን፤ ከመሐከላችን አንግዳ አሰፋው ተስፋ ቆርጦ ወደ ኩሎ ሄደ።

ሰኔ 8 ቀን 1944 ዓ.ም ታሪክ ተሰወጠ፡፡ በዕስቱ ከሰዓት በኋላ አንድ ልጅ አንድ ደብዳቤ ስሚልደረድ ሂስታንድ አመጣሳት። እንዲህ ይል ነበር፤ "ነገ ሰኔ 9 ቀን





44 ዓ.ም. ሂሳብና ሶሺያል ስተዲስ፣ ከነገ ወዲያ አማርኛና እንግሊዝኛ ስለሚፈተኑ ተፈታኝ ተማሪዎች ወደ መንግስት ትምህር ቤት በጠዋት እንዲመጡ"።

ተስፋችን እንሰራራ፤ ከምን ጀምረን ወዴት እንደምንሄድ ግራ ገባን፤ ተደነባበርን። የአንግዳ አሰፋው ወላጆች ከለገ ኩሎ ሰው ልከው በቶሎ እንዲያስመጡት ነገርን። የቀረነው አምስታችን ማለት ጸጋ ወ/ማርያም፣ አብዱልዋሲ አደም፣ አብዱስቡር ዩሱፍ፣ ጥላሁን እበበ እና እኔ ለሊቱን ሜት እየቃምን ስናጠና ልናድር አብዱልዋሴ ቤት ተሰበሰብን።

በማግሥቱ ለፈተና ተቀመጥን፡፡ ስማችንንና ትምህርት ቤታችንን ደደር የመንግሥት ትምህርት ቤት ብለን እንድንጽፍ በተነገረን መሠረት አደረግን። የፈተናው ቅደም ተከተል በደብዳቤው እንደ ተገለጸልን ነበር፡፡ ፈተናውን ከጨረስን በኋላ የጥያቄዎቹ መልስ ምን ምን እንደነበር ተጠያይቀን ምን ያህል እንደሰራን በመጠኑ ተረዳን፤ ውጤታችንን በታላቅ ናፍቆት መጠባበቅ ጀመርን።

የውጤቱ መምጫ በቆየ ቁጥር ስጋታችን ጨመረ፡፡ ተፈታኞቹ ተሰብስበን ተማከርን ወደ ሐምሌ ወር መጀመሪያ ሳይ ወደ ሚልድረድ ሂስታንድ ሄድን፤ "ፈተናውን የምናልፍ አይመስለንም፤ እንደ ፖሊስ ካዴት ያለ ትምህር ቤት ገብተን ለመማር ስለምንፈልግ ሰርተፊኬት ስጪን" አልናት። "የሙያ ኮርስ ከፈለጋችሁ ሚሲዮናችን ናዝሬት ሳይ የድሬሰርና የመጽሐፍ ቅዱስ አዳሪ ትምህርት ቤት ሲከፍት ነው፤ ለትምህርት ቤቱ ምንም አይከፈልም፤ ማደሪያም ምግብም በነጻ ይሰጣል፤ እዚያ ሄዳችሁ ብትሰለጥኑ ሙያ ትማራላችሁ" አለችን።

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ኮርሱ ለማወቅ ምንም ጉጉት አላሳየንም፤ ሁላችንም በአንድነት ድሬሰር ኮርስ ምንድነው? ምንድን ነው የምንማረው? ምንድን ነው የምንሆነው? በማለት ጠየቅናት። ልታስረዳን እንደ ሞከረች አስታውሳለሁ፤ በሃኪም ቤት ዉስጥ ሥራ ልናገኝ እንደምንችል ነገረቺን፤ ደደር ሃኪም ቤት የሚባል ድሬሰር የሚል ቃል ሰምተን አናውቅም፤ ስለዚህ የምትለው ምንም ሊገባኝ አልቻለም። ድንገት ብልጭ አለልኝ "እንደ ጋሼ ታደሰ?" አልኩ፡ በደደር ከተማ አንድ ከሊኒክ ውስጥ ነጭ ካፖርት ለብሶ ጎርደድ ጎርደድ የሚል ሐኪም

ታደሰ የሚባል ሰው ነበር። "አዎ" አለች:: ምንም ሳላመነታ "እኔ አፈልጋለሁ" አልኩ:: ቀስ በቀስ ሌሎቹም በሃሳቡ ተስማምተው የመማር ፍላጎታቸውን ስለ ገለጹ እንድታስመዝግበን ነገርናትና ያገኘነውን ዕድል ለየወላጆቻችን ለማብሰር ተስማምተን ተለያየን።

ያኔ እባብዬ (እባቴ) መንዲሳ ነበር፤ ወደ ሐረርቲ ወርጄ ለእባዬ ነገርኳት:: ት/ቤቱ ናዝሬት ላይ መሆኑን፤ ናዝሬት የት እንደሆነ ስለማታውቅ አዲስ አበባ እጠገብ ሸዋ ዉስጥ እንደሆነ፤ እዳሪ ትምህርር ቤት መሆኑን፣ ምግብና ማደሪያ እንደሚሰጠን ነገርኩዋት። ለመደበቅ ብትሞክርም የደነገጠች ትመስላለች "እሰቲ ነገ መንዲሳ ሂድና ለእባትህ አማክረው" በማለት ለጊዜው ተገላገለችኝ::

ከሐረርቲ መንዲሳ ሄጄ ለእባብዬ ስነግረው ምንም ሳያቅማማ በሃሳቤ ተሰማማ፡ እልፎም "ጥሩ ነው ታዲያ መቼ ነው መሄድ ያለባችሁ?" ከእለኝ በኋላ፡- "በል እንግዲያው እብዱል ጀማል ዘንድ ሄደህ ከአማሪካን ካኪ ጨርቅ ባንጠሎንም ሱሪና ኮት እንዲሰፋልህ ነገረው" እለኝ። በጣም ተደሰትኩ ኩራት ተሰማኝ:: ቁምጣ ሱሪ ለባሽ የነበርኩት ልጅ በድንገት ረጂም ሱሪ ልለብስ ነው?! ባንጠሎን ሱሪ ደግሞ ጫማ ስለ ሚያስፈልገው እንደሚገዛልኝ አርግጠኝነት ተሰምቶኛል። ገና ሳልለብሰውና ሳልጫማው ደስታው ሊገለኝ ደረሰ:: ድሬሰር ትምህርቱ የሚጀምረው ነሐሴ 1 ቀን 1944 ዓ.ም. እንደሆነና ቀደም ብለን ብንሄድ መልካም መሆኑ ተነገረን:: ባንጠሎን ሱሪውና የሳሪያን ኮቱም ከች እለ፤ አንድ የምታምር ሸራ ጫማም ተገዛልኝ፤ ደስታዬና ኩራቴ ከፍ ከፍ ሲል ይታወቀኛል::

ሐምሌ 21 ቀን በጠዋት ተንስታ እባዬ ጓዳ ገብታ፣ ብዙ ቆይታ ወጣች፤ ለምን ጓዳ እንደ ቆየች አልገባኝም ነበር። በኋላ እንደ ነገረችኝ እያለቀሰች ለማርያም ስትሳል ነበር፤ (ደደርን የለቀቅሁት የማርያምለት መሆኑን ልብ ይሏል)። የእናቴ ስዕለት ይህ ነበር፡-

"እምዬ ማርያም፣ ልጄን ለወግ-ማአረግ አብቂልኝ፣ ጠብቂልኝም፤ እስከአዚያ ድረስ እኔ ጠበል ጠዲቅሽን በታማኝነት አወጣለሁ::"





ማልቀሷን እንዳላውቅ አንባዋን ዋጥ እድርጋ ተሰናበተችኝ፤ ያኔ እከሊልን እርጉዝ ነበረች። እህቴ እሰገደች፣ እከስቴ እባዬ፣ ብዙዬና ሌሎች ዘመዶች ደደር አውቶቡስ ጣቢያ ድረስ መጥተዉ እያለቀሱ ተሰናበቱኝ።

አራታችን፡- ጺጋ ወልደ ማርያም፣ እንግዳ እስፋው፣ ጥላሁን እበበ እና እኔ ሆነን፣ ሐምሌ 21 ቀን 1944 ዓ.ም ደደርን ለቀቅናት:: ጨለንቆ ቆም ብለን ጉዞ ቀጠልን፤ ቁልቢ ልንደርስ ስንል ቢምበረድ የምትባለዋን ገደል ቦታ ስናልፍ በደህና እንዲያሻግረኝ ለቁሉቢ ገብርኤል የሃምሳ ሳንቲም አጣን ልሰጠው ተሳልሁ፤ (እስካሁን ስለቴን አልከፈልሁም!):: ቀኑን ሙሉ በኩሬራ (የዚያን ጊዜ አውቶቢስ) ስንጓዝ ውለን ድሬ ዳዋ ገባን። ድሬዳዋ እንደ ገባን ጓደኞቻችንን አፈላልገን አገኘን፤ በእነርሱ እርዳታ በእንድ ከፍል ዉስጥ አራት እልጋ ያላት አልቤርጎ ያዝን፤ ከጓደኞቻችን ጋር ስንጨዋወት አምሽተን ለመኝታ ወደ አልቤርጎአችን ገባን::

አንዲት እምፖል ለእኛና ለሚቀጥለው ከፍል ብርሃን እንድትሰጥ ተንጥልጥላለች። የኢለትሪክ አምፖል መብራት ሲሰጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ማየቴ ነው። አምፖልዋ ከፍ ብላ ስለ ተንጠለጠለች እንዴት ደርሰውባት እንደሚያጠፏት ለማየት ዐይኔን ከፍቼ በመጠባበቅ ላይ እያለሁ እንቅልፍ ወለደኝ፤ ጠዋት ስነቃ እምፖልዋ ጠፍታ አገኘኋት፤ እንደ ኩራዝ እፍፍ ብለው የሚያጠፏት መስሎኝ ነበር፤ ያኔ ማብሪያ ማጥፊያ እንደ እለ እንኳን አላውቅም ነበር ማለት ነው::

***

በማግስቱ ጠዋት ድሬዳዋ ያለውን የሚስዮን ኃላፊ ልንጎበኝ ሄድን። በጉብኝታችን ወቅት አሳፋሪ ነገር አደረግን:: ወደ ናዝሬት ልንሄድ ከደደር አንደ መጣን ነገር ግን ለባቡር የምንከፍለው ገንዘብ ስለሌለን እንዲሰጠን ጠየቅነው፤ እስፈላጊውን ወጪም ሸፈነልን:: በድርጊታችን ወዲያውኑ የሐፍረትና የፀፀት ስሜት ጀመረኝ። በበኩሌ ይህን የነለና ከስ የተገላገልኩት ከብዙ ዓመታት በኋላ ከተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት እንደ ተመረቅኩ፣ ኃጢአቴን ተናዝዤ ገንዘቡን ለሰጡኝ ለሚስተር ሲንስኒንግ በመሰስኩበት ጊዜ ነበር::

ወደ ጉዞአችን ነገር ልመለስና፣ ማታ ነበር ከድሬደዋ የተነሳነው፤ በባቡሩ የኋላ አቃ መጫኛ ፉርጎ ተሳፍረን ወደ ናዝሬት ጉዞ ጀመርን። በማግስቱ ሲነጋጋ ናዝሬት ገባን። እንደገባን ሆስፒታሉ የት እንደሆን አጠያየቅን:: "እናሳያችሁ ስንዱቃችሁን (ከንጨት የተሰራ ሻንጣ) አንሸከምላችሁ" የሚሉ ወጣቶች አዋከቡን:: ያው ባላገሮች ነንና አብዛኞቻችን ግራ ተጋባን፤ ከሁላችን የተሻለው እኛን ወክሎን የሚደራደረው ጥላሁን እበበ ነበር። "እሺ ታዲያ ስንት ታስከፍሉናላችሁ?" ሲላቸው። "ሁለት ሁለት ዱንቡሎ" አሉት:: ሁላችንም "ድንቡሎ ምን ማለት ነው?!" በማለት ግራ ተጋባን:: እንዲያውም "ድንቡሎ" ሙልሙል ዳቦ መስሎን ነበር:: ጥላሁን ፈጠን ብሎ "እኛ ድንቡሎ የለንም፣ ስንት መሃለቅ እንደምትፈልጉ ንገሩን" አላቸው፤ ዱንቡሎ አስር ሣንቲም መሆኑን ሹፈት ባዘለ ሣቅ ሲያስረዱን ተስማማን:: አዲስ የናዝሬት ቃል ተምረን ሆስፒታሉ የጀርባ በር ደረስን::

አንድ ጠቆር ያሉና በጨርቅ የተሸፈነ መጽሐፍ በብታቸው ሥር የያዙ ዘበኛ መጥተው ስምን እንደ መጣን ጠየቁን። ከዚያም "ፈረንጆቹ ገና አልተነሱም፤ እስኪመጡ እዚህ ዛፍ ሥር ሆናችሁ ጠብቁ" አሉን። እኚህ ሰው ሜኖናይቶች እርዳታ ለመስጠት ግቢዉን ከመንግሥት እንደ ተረከቡ ስጥበቃ የተቀጠሩ ዘበኛ ነበሩ:: ባቲ እንስርሙ ይባላሉ፤ ሲቀጠሩ ሙሐይም ነበሩ ሚሲዮናውያኑ ማንበብና መጻፍ አስተማሩአቸው::[1] ስናገኛቸው በብብታቸው ስር የያዙት መጽሐፍ ቅዱስ ነበር። ሌሊቱን በጥበቃ ላይ ስለሚያድሩ በልዩ ልዩ ቦታ ባሉ መብራቶች ሥር ቁጭ ብለዉ ያን መጽሐፍ ቅዱስ ያነቡ ነበር:: ጌታ ኢየሱስን እንደ መድህናቸው ተቀበሉ፤ በእና ባፕቲስት አስተምህሮ መሠረት የውኃ ጥምቀት ከፈጸሙት ከመጀመሪያዎቹ አንዱ ሆኑ፤ ከመጀሪያዎቹ የመሠረተ ክርስቶስ አባላት ዘንድ ይቆጠራሉ።

[1]1 ከብዙ አመታት በኋላ አሜሪካን አገር ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ናዝሬት በሚስዮናዊነት የመጡትን ሎሬታ ሜየርን አግኝቼ ለአቶ ባቲ እንዴት እንደ መሠከሩላቸው ሲነግሩኝ እንዲህ ብለው ነበር፤ "በወቅቱ አቶ ባቲ ማንበብ አይችሉም ነበርና ወንጌልን ሰጥቼው ዮሐ 3፡16 እንዲያነብ ማድረግ አልቻልኩም፤ እኔ ደግሞ አማርኛ ባግባቡ ስለማልችል የሰው እርዳታ ያስፈልገኝ ነበር። ስለዚህ ዮሐ 3፡16 በአማርኛ እንግሊዘኛ እንደሚከተለው አጻፈችና Egzihabher endihu alemn wedoalna and ljun eskisett dreses. Bersu yamene hulu endayttefa yezelalem hywet yhonlet enji ደጋግማ በማንበብ አጥንታ ለአቶ ባቲም በቃሏ ደገመችላቸው አቶ ባቲንም ከእርሷ በኋላ እንዲደግሙ በማድረግ አስጠናቻቸው:: ሜኖናይቶች ወንጌል ለአገሬው እንዲገባ የነበራቸውን ናፍቆት ለመገንዘብ ያስቻለኝ ታሪክ ነበር::
1 ሶተሊ:- የጆንሶ መስሪያ ክር





ወደ ትውስታዬ ልመለስና፤- ሆስፒታሉ ወጥ ቤት አጠገብ ተቀምጠን አቶ ባቲ ፈረንጆቹ ከመኝታ እስኪነሱ ድረስ ሲመሰከሩልን ጀመሩ:: ምን ምን ይባባሉ እንደ ነበር አላስታውስም ከጥላሁን ጋር ግን ስለሃይማኖት ሲከራከሩ ትዝ ይለኛል:: በጣም ደክሞኝ ስለነበር ሸለብ አደረገኝ:: ከጥቂት ቆይታ በኋላ የወጥ ቤቱ ኃላፊ (አቶ ከበደ መሆኑ ነው) ሻይ በፊንጃል ሰጠንና አሞቀን፤ በሁዋላም ሚስተር ዌንገር መጡና ተቀበሉን፤ ከፍላችን ስላልተዘጋጀ ሳጥናችንንም የምናሳርፍበት ቦታ አሳዩን። በአዲሱ ትምህርት ቤት ለመማር ከመጡት የመጀመሪያዎቹ ነበርን።

ሲመሽ በአንድ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ የብረት አልጋዎች ተደረደሩ። አራት ከበሉን በሁዋላ ሚስተር ዌንገር ጥቂቶቻችንን ከሆስፒታሉ ፍራሽ እንድናመጣ ይዘውን ሄዱ:: ወደ አንድ ከፍል እንደገባን ብርሃን በራ፤ ልክ ድሬዳዋ እንዳየሁት ያስ ተንጠልጣይ ነገር ነበር የብርሃኑ ምንጭ:: ይህን ብርሃን እንዴት እንደሚለኩስና እንደሚጠፋ የማወቅ ጉጉቱ እንደ ገና ተቀስቀሰብኝ:: እብረን ከነበርነው ሁለቱን ልጆች በአልጋው ላይ የነበሩትን ፍራሾች ይዘው እንዲወጡ አዘዙና የቀረነው ወደ ሌላ ከፍል ሄድን፤ መብራቱ እንዴት እንደሚለኮስ ለማየት ሚስተር ዌንገርን በትኩረት እየተከታተልኩ ነበር:: በግድግዳው ላይ የተለጠፍቸውን ነካ ሲያደርጓት መብራቱ በግ ብሎ ሲበራ አየሁ:: ስንወጣም ያችኑ ነገር ነከተው እንዳጠፉት ተመለከትኩ::

በማግስቱ ጠዋት ተነስቼ ወደ ከፍሎቹ ሄድሁ፤ ግድግዳው ላይ የተለጥፉ ነገሮች አገኘሁ፤ ኤሌክትሪክ ይይዛል ሲሉ ሰምቼ ነበርና ብነካው ይይዘኝ ይሆን ብዬ ፈራሁ፤ ደግሞ መያዝ ምንድን ነው? እንዴት ይይዘኛል? ከመያዝ ፍርሃቴ የማብራት ጉጉቴ ስላየለ በሰሱ ነካ አደረግሁት፤ ምንም አላደረገኝም፤ ስደባብስ አንድ ነገር ቀጭ አለ! ከቀጭታው ድምጽ እኩል መብራቱ በራ! ደግሜ ቀጭ ጠፋ! ትልቅ ድል ኤሌክትሪክ አብርቼ አጠፋሁ! በጣም ተደሰትኩ! ደስታዬ ኤሌትሪክን ከፈ.ለሰፈ.ው ቤንጃሚን ፍራንክሊን ደስታ እይተናነስም ነበር:: ከአንድ ዓመት በኋላ የኤሌትሪክ ባለሙያ ሆንኩ። በእኔ ደረጃ ትልቅ የዕውቀት ምጥቀት መሆኑ ነበር::

***

## ሦስቱ

## የድሬሰርና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መጀመር

ነሐሴ 1 ቀን 1944 ዓ.ም እራታችንም የድሬሰርና የመጽሐፍ ቅዱስ ኮርስ ጀመርን። የድሬሰር ኮርሱን የሚያስተምሩን ነርሶችና ዶክተር ኤሽልመን ሲሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቱን የሚያስተምሩን ደግሞ ሚሰተር ዌንገር ነበሩ፡፡

እንዳንድ ብር እንድንከፍል ተደረገና ሁላችንም መጽሐፍ ቅዱስ ተሰጠን። የግሌን መጽሐፍ ቅዱስ ስላገኘሁ በጣም ተደሰትኹ። የሚስተር ዌንገር መጽሐፍ ቅዱስ ማስተማር ዘዴም ግሩም ነበር፡፡ የቤት ሥራ ሲሠጡን ጥያቄዎችና መልሳቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ የት እንደሚገኝ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጽፉልናል። ማደሪያችን ሄደን መጽሐፍ ቅዱስ እንብበን ለጥያቄዎቹ መልስ እንጽፉለን። አብዛኛውን ጊዜ የቤት ስራ የሚሰጡት የኔ ጥያቄዎች ስለነ በሩ መልሳቸውን ለማግኘት አጥር ነበር፡፡ ጽፌ የመጣሁትን መልስ ከሚስተር ዌንገር መልስ ጋር ለማስትያየት አጓጓሰሁ፡፡ ብዙ አከራካሪም ነበር። ከንባብና ጥያቄና መልስ በተጨማሪ ብዙ ጥቅሶች በቃል እንድናጠና ይደረግ ነበር፡፡ በቃል ካጠናናቸው ጥቅሶች መካከል 1ኛ ቆሮንቶስ 13 ሙሉው ምዕራፍ ይገኝበታል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የሚሰጠው ማሰዳ ላይ ሲሆን፤ የድሬሰር ትምህርት ደግሞ ከረፋድ ጀምሮ ከሰአት በኋላና ምሽትም ነበር፡፡ በሆስፒታሉ በምንማርበት ወቅት የጽዳት ሥራ፣ የሕመምተኞችን አልጋ ማንጠፍና የመሳሰሉት የመጀመሪያ ትምህርት ነክ ተግባራታችን ነበሩ፡፡ እያደር ከእኛ በትምህርትም በልምድም ከፍ ያሉቱ (ሲኒየር) ድሬሰሮችና ነርሶች አዘጋጅተው የሚሰጡንን መድኃኒት ለሕመምተኞች ማደል ጀመርን። ቀስ በቀስ ደግሞ ቅድመ ሕክምና ምርመራ ማለትም ትኩሳት፣ ትንፋሽና የመሳሰሉትን መሰካት ጀመርን፡፡ ትኩሳት የምንሰካው ቴርሞ ሜትሩን በሕመምተኞቹ ምላስ ሥር በማድረግ ሲሆን ራሳቸውን የማያዉቁ ከሆነ በብብታቸው ስር በማስያዝ ነበር።





አንድ ቀን የወባ በሽታ ይዞት ራሱን ስቶ የመጣ ሕመምተኛ አጋጠመኝ፤ ሙቀቱን ለመለካት ቴርሞ ሜትሩን ምላሱ ሥር አድርጌለት ለደቂቃዎች ያህል ወደ ሌላ ቦታ ሄጄ እንደ ተመለስኹ "አፍህን ከፈት" አልኩት፡፡ አፉን ሲከፍት ያየሁትን ማመን አቅቶኝ በድንጋጤ እየተርበተበትኩ ጓደኛዬን ኩተማ! ከተማ! ብዬ ተጣራኹ። ከተማ ሰውዬውን አይቶ ድንጋጤዬ ተጋባበት፡፡ ሰውዬው ቴርሞ ሜትሯን ቁርጥምጥም አደርጓታል፡፡ ጭራሽ ሰባሪዋ ጉሩሮው ላይ ተሰንቅራለች። ከተማ ሕመምተኛውን ከተጋደመመበት ቀና አድርጎ የበሽተኛውን ማጅራት መታው፤ ሜርኩሬዋ ፈትልከ ብላ ወጣች፡፡ እሰይ! ሰውዬው ሳይሞትብኝ ቀረ።

ለድሬሰርነት የምንሠለጥነው ተማሪዎቹ የመጣነው ከተለያዩ ቦታዎች፣ ማሕበረሰባዊና ባህላዊ ዳራዎች ነበር፡፡ እራታችን ከደደር፣ እነ በየነ ሙላቱ ከአዲስ አበባ፣ እነ አሰፋው ባቼሬ ከዱራሜና ከሆሣዕና፣ እነ ገብረ ሥላሴ ሐብታሙ ከፍቼ (ስራዊተ ክርስቶስ ማህበር) ነበሩ። ከሠራዊተ ክርስቶስ የመጡት በዲቁና፣ በቅስና ያገሰገሉ ስለ ኦርቶዶክስ እምነት ጠንቀቀው የሚያውቁ ነበሩ፡፡ በተጨማሪ የታላቁ የሠራዊት ክርስቶስ ሚሲዮናዊ የዴቪድ ስቶክስ ደቀ መዝሙር ነበሩ፤ አክራሪ ኦርቶዶክሶች የሆነው እነርሱ የሚሉትን በእንክሮ እንሰማቸው ነበር። አንድ ቀን ጋሼ ገብረ ስላሴ፣ ላህሴና አንድ ሌላ ተማሪ ቆመው በሹክሹክታ ሲነጋገሩ ጆሮዬን ጣል አድርጌ አሰማቸው ነበር፤ "የእኛ ቤተ ክርስቲያን ከዚያች ነገር በስተቀር እኮ ደህና ነበረች" ሲሉ ሰማሁ። ምንድን ናት ያች ነገር ግራ? ገባኝ!፡፡ ጠጋ አልኩና 'ከዚያች ነገር ስትሉ ምን ማለታችሁ ነው? አልኳቸው። "ያን ትልቁን ነገር ነዋ" አሉኝ ወደ ጭንቅላታቸው እያመለከቱ፡፡ ምንድን ነው የሚሉት? የበለጠ ግራ ገባኝ፤ ጥቂት አሰብ አድርጌ የገባኝ የመሰለኝን እያመነታሁ ታቦቱን?! ብዬ በቁጣ መልክ ጠየቅኋቸው፤ መልስ ከመስጠት ይልቅ በነገሩ እንዳስብበትና እንድመረምር መከረውኝ ተለያየን።

***

እራታችን የደደር ልጆች የድሬሰሩንም የመጽሐፍ ቅዱሱንም ትምህርት በትጋት መከታተል ቀጠልን። አከራሪነታችን ለሚለዩኑ ጥቂት አሰቸጋሪ ሳይሆን

አልቀረም፤ ሌሎች ተማሪዎች በተለያዩ ቀናት የተረዱትን ይናገራሉ፤ የሚሉት እምብዛም አልገባንም። አንድ ቀን አንድ ቄንጠኛ ወጣት ከአዲስ አበባ መጣ፤ ጠጉሩ እንደ ፈረንጆች ከፍሎ ደልሶታል፤ ተክለ ሰውነቱ ስፖርተኛ ነው:: ስሙም በየነ ጭጭ አይበሉ ይባላል::

የመጣ ለት፤ ማታ ማታ በሚኖረን ፕሮግራም ላይ ተናጋሪ ነበር:: ያን ምሽት እኔ ሆስፒታል ተረኛ ስለ ነበርሁ መለማት አልቻልኩም፤ በማግስቱ ጸጋ ወ/ማርያምን እንዲነግረኝ ጠየቅሁት:: "አሆ፤ ልጁ እሳት ነው!" የሚል መልስ ሰጠኝ:: የበለጠ እጓጓኝ "ምን አለ? ምን አስተማረ?" ብዬ ጠየቅሁት:: "ተቀብዬዋለሁ! ይላል" አለኝ። "ምኑን ነው የተቀበለው?" ስለው "የፈረንጆቹን ሃይማኖት ይሆናላ" አለኝ። ክርስቶስን ተቀብዬዋለሁ ማለቱ አልገባንም ነበር::

ወደ መስከረም መጀመሪያ ላይ ከአራታችን በስተቀር ሌሎች ሁሉም እየተነሱ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል:: ያልመሰከርን እኛ አራታችን ብቻ ነበርን:: አንድ ቀን ጥላሁን ተነስቶ ተናገረ ቁጥራችን ተሸረሸረ:: ይባስ ብሎ እንግዳ ቀጠለ፤ ቁጥራችን ጭራሽ ተመናመነ:: ከዚያ በኋላ እነርሱ ምን እንዳሉ አላለታውስም፤ እኔ የምናገረውን ሳሰብ ነበር፤ ተራዬ ሲደርስ ብድግ በዬ በአገኘሁት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ደስተኛ መሆኔን ገለጽሁ:: ከእኔ በኋላ ጸጋ ተናገረ። ከዚያ በኋላ አከራሪ መሆናችን እየቀነሰ ሄደ።

***

አንድ ቀን ከደደር አንድ ሰው መጣ። የሁለተኛ ደረጃ መግቢያ ፈተናውን ከተፈተንነው ውስጥ ሁለት እንዳለፍን ጭምጭምታ ተሰምቷል ብሎ ነገረን። አንዱ ጸጋ ለመሆኑ እርግጠኞች ነበርን፤ እርስ በእርሳችን ሁለተኛው አንተ ነህ! አይ አንተ ነህ! ለንባባል ቆየን። ብዙም ሳይቆይ "ጸጋና ሚሊዮን የሁለተኛ ደረጃ ፈተና ስላለፋችሁ ወደ ሐረር መሄድ ስላለባችሁ ቶሎ ወደ ድሬዳዋ እንድትመጡ" የሚል ቴሌግራም ደረሰን። ተሌ ግራሙን ድሬዳዋ ድረስ በመምጣት የላኩልን የጸጋ አባት ነበሩ።






ቴሌግራሙ የደረሰን ዕለት እንግዳና ጥላሁን አዝነው አልጋቸው ውስጥ እንደዋሉ አስታውሳለሁ። በየነ ሙላቱ "እንደምትሄዱ ያዋቅሁትና ተስፋ የቆረጥሁት ያኔ ሁለት አልፋችኋል በተባለ ቀን ነው" አለኝ። ቴሌግራሙን ይዘን ወደ ሚስተር ዌንገር ሄድን ነገርናቸው። መሄዳችንን ባይደግፉም ምሳሌ 3:5-6 "በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን አወቅ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል" የሚለውን እንዳነብ ጠየቁኝና ይህን




ለከፍተኛ ትምህርት ሐምሌ 21 ቀን 1944 .ዓ.ም በሰቃሶ ወደ ሸዋ የተሸኙት አራቱ ደደሮች።

ጥቅስ የሕይወታችን መመሪያ አድርገን እንድንወስድ መከረው አስናበቱን። እንግዳንና ጥላሁንን ናዝሬት ትተን ወደ ድሬዳዋ ሄድን።

የተጠራንበትን ደብዳቤ ይዘን ወደ ሐረር ሄደን፤ ሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት ት/ቤቶች ዋና ሥራ አስኪያጁ ፊት ስንቀርብ፤ ወደ አዲስ አበባ እንደምንሄድ ነገሩን። እዚያው ሐረር መድኃኔ ዓለም ሁለተኛ ደረጃ የምንገባም መስሎን ነበር። ደብዳቤ አስይዘው ወደ አዲስ አበባ ላኩን።



ጥላሁን አበበ፣ፀጋ ወ.ማርያም፣ እንግዳ አስፋው እና ሚሊዮን በለጠ በ 1948 .ዓ.ም

# ምዕራፍ 2

# ወደ አካዳሚክ ሕይወት

## አዲስ ጅማሬ - በአዲስ አበባ

አዲስ አበባ እንደ ደረስን የፓርላማ አባል የሆኑት የአባቴ ጓደኛ ስድስት ኪሎ እንደሚኖሩ ሰምቼ ስለ ነበር ጋሪ ተከራይተን በፊት በር በኩል ወደ ስድስት ኪሎ አመራን:: የፊት በርን ዳገት ፈረሱ ሶስታችንና ሰንዱቃችንን ይዞ መውጣት ስላቃተው ባለ ጋሪው ወረደና ዳገትዋን ወጣናት። ስድስት ኪሎ አካባቢ የአቶ ተክለማርያም ወልደ ሐዋርያትን ቤት እጠያይቀን አገኘነው:: እኩያዬ የነበረው ልጃቸው ግርማ ተክለ ማርያም ተቀብሎኝ ሰንዱቃችንን እዚያ አስቀምጠን ወዲያው ወደ ትምህርት ሚኒስቴር ወሰደን።

የያዝነውን ደብዳቤ ሰጠንና የተመደብነው ተግባረ ዕድ ት/ቤት እንደሆነና ከሰአት በኋዋላ በመኪና እንደምንወሰድ ተነገረን። በፈተናው ያገኘነውን ማርክ ማውቅ ከፈለግን ሲነገረን እንዳሚቻል ስለተረዳን ወደ ዋናው ኢኒስፔክተር ወደ አቶ መኮንን ዘውዴ ሄድን። እኔ በቁጠር (ሂሳብ) 93%፣ በእንግሊዝኛ 44%፣ በሶሻል ስተዲስ (ያኔ የኅብረተሰብ ትምህርት ይባል ነበር) 48%፣ በአማርኛ 53% እንዳገኘሁ ተነገረኝ። የሰከንደሪ ፈተናውን ያሰፍኩት በቁጥር ጎበዝ በመሆኔ እንደሆነ ተረዳሁ::

ቀደም ብሎ እንደ ተነገረን ከሰዓት በኋላ በአንድ ቮልቮ የጭነት መኪና ተሳፍረን ተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ተወሰድን። ወዲያው ደደር ተማሪ የነበረ ድሬዳዋ መጥቶ ተፈትኖ በማለፉ እዚያው ተግባረ እድ ትምህርት ቤት ቀድሞን የገበውን ኃይሴ ወ/ማርያምን (አሁን ኮሞዶር) እንደገባን አገኘነው;: ኃይሌ ቶሎ





ከትምህርት ቤቱ ሥርዓቶች ጋር አስተዋወቀን። የተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ተማሪ ሆንኩ፤ አዲስ ሕይወት ተጀመረ::

***

ምሽት አካባቢ የእራት ጊዜ መድረሱን የሚያበስረውን ደወል ሰምተን ወደ ምግብ ቤቱ አዳራሽ አመራን:: አዳራሹ ውስጥ ስንገባ በግራ በኩል ለአንደኛ አመት ተማሪዎች የተመደበ ረዥም ጠረጴዛ ነበር:: መካከል ላይ ለሁለተኛና ሦስተኛ አመት ተማሪዎች የተመደበ ጠረጴዛ እለ:: ከጀርባ አራት ሰው የሚያስቀምጡ ነጭ ልብስ የለበሱ ጠረጴዛዎች ለምሕንድስና ኮሌጅ ተማሪዎች የተመደቡ ነበሩ። (ግቢው ውስጥ የምሕንድስና ኮሌጅ የተጀመረበት ዓመት ነበር)። ሁላችንም ጠረጴዛችን ላይ እንደ ተቀመጥን ምግብ እዳያችን በትልቅ ብረት ድስት ምግቡን ይዞ መጣ፤ በየሳህናችን ላይ አወጣልን:: በስጎ የተለወሰ መኮሮኒ፣ ቀይ ስር፣ ድንችና ካሮት ነበር:: ጣእሙ ልዩ ሆነብኝ። ኃይለ ማርያም ማሞ መታሰቢያ ሆስፒታል የለመድኩት አይነት አልነበረም:: ምርጫ አልነበረኝም ራሴን ማስለመድ እንዳለብኝ አሣምኜ እንደ ምንም የተሰጠኝን ጨረስሁ::

በማግስቱ ቅዳሜ የአዲስ አበባን ከተማ ከኃይሌ ጋር ለመጎብኘት ወጣን:: ወደ ፒያሳ ስንሄድ ትኩረታችንን አንድ ሕንፃ ወሰደው፤ ሕንፃው ላይ የጦርና ጋሻ ምልክት አለበት:: በአድናቆት የተመለከትነው የጦር ሚኒስቴርን ነበር:: በዚያን ጊዜ የጦር ሚኒስቴሩ ራስ አበበ አረጋይ ነበሩ:: የቸርቺል ጎዳና ዳገትን በእግር ፉት ብለናት ፒያሳ ደረስን:: ፒያሳ የደረስነው በስምንት ሰዓት ስለ ነበረ በየበረንዳው ብዙ ሰው ተኮልኩሎ በማየታችን ተገረምን:: የአዲስ አበባን ራዲዮ መጀመር እየተጠባበቁ መሆኑ ነበር::

ከደቂቃዎች በኋላ አንድ ምሰሶ ላይ የተሰቀለው የድምጽ ማጉያ የራዲዮ ፕሮግራሙን ለመጀመር ዋሽንት ድምጽ አሰማ። ራዲዮ ስሰማ ይህ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር፤ በአድናቆት አዳመጥን:: ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እንደዚህና እንደዚያ አደረጉ የሚሉ በዛ ያሉ ወሬዎችን ካሰማ በሁዋላ ያለም ዜና መሰማት

ተጀመረ። «የእንግሊዙ ንጉሥ ጆርጅ ከዚህ ዓለም በሞት ስለ ተለዩ ልጃቸው ልዕልት ኤልሰቤጥ የታላቋ ብሪታንያ ንግሥት ሆኑ፣» ሲል ከአወራ በኋላ ወዲያው ዘፈን ማሰማት ጀመረ፤ ሁሉንም ዝግጅት ለአንድ ሰዓት ቆመን አዳመጥን። ልክ እንደ አምፖሏ፥ ሬዲዮ ለመጀመሪያ ጊዜ ማዳመጥም ለእኔ አስደናቂ ተሞክሮ ነበር።

ከዚያ በኋላ ኃይሌ የወሰደን ወደ ዳግማዊ ምንሊክ አደባባይ ነበር፤ አምዬ ምንሊክ የፊት እግሩን ነቅሎ፣ ሰመፈንጠር በኋላ እግሮቹ ብቻ የቆመው ፈረሳቸው ላይ ጉብ ብለው በማየታችን በጣም ተደነቅን። ከዚያ በኋላ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘውድ የጫኑበትን መናገሻ ጊዮርጊስን ጎበኘን። ቀጥሎ የአቡነ ጴጥሮስን ሐውልት አየን። በሐውልቱ ላይ የተጻፈውን የአደራ ቃልም አነበብን። አስደሣች ጊዜ ነበር።

***

ለኞ ጠዋት ወደ ዲሬክተሩ ቢሮ ሄድን፤ የክፍል ምድባችን 3C መሆኑ ተነገረን፤ ተወዳጆቹ የቴክኒክ ክፍሎች እንደ ሞተርና ማሺን ሾፖች በመሙላታቸው ከራዲዮና ከአናጢነት እንድንመርጥ ተጠየቅን። ራዲዮ ሾፕ መረጥን። ወደ ግምጃ ቤት ሄደን መጻሕፍትና ደብተር እንድንወስድ ተሰጥቶን ወደ ክፍላችን (3C) ገባን።

ተማሪዎቹ ከልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶችና ከተሞች የመጡ ነበሩ። ብዙዎቹ አነጋገራቸው፣ አኳኋናቸውና ጮሌነታቸው አስፈራኝ። ከእነዚህ ብልጥ ልጆች ጋር እኩል ተምሬ በውጤት እንደማልደርስባቸው ይሰማኝ ጀመር።

የራዲዮ ሾፕ መምህራችን እግሩ ላይ የአካል ጉዳት ያለበት እያነከሰ የሚሄድ ሕንዳዊ ነበር። ክፍል ስንገባ የተቀበለን ድምጹን ከፍ አድርጎ ነው (NOW!) በማለት ነበር። ሲያስተምር ይቆጣል። ይህን እድርጉ፣ አታድርጉ፣ ማለትም





ያበዛል። እኔና ጺጋ የራዲዮ አስተማሪአችንን ቁጡ ባህርይ ተቀብለን የራዲዮ ትምህርታችንን ጀመርን። የትምህርቱ አሰጣጥ ጠዋት ጠዋት መደበኛ ትምህርት ሆኖ ከሰአት በኋላ በሾፕ ነው። ትምህርት አወሳሰዳችን ከክፍል ወደ ክፍል እየተዘዋወርን ስለነበር አስገራሚ ነገር ነበር የሆነብኝ። በተለይ ለሳይንስ በጣም ተስማሚ ነበር። ከሁሉም የትምህርት አይነቶች ፊዚክስ አወድ ነበር በፈተና (test) ጥሩ ውጤት ማግኘቴ ደግሞ ይበልጥ አደፋፈረኝ። መምህሩ ሚስተር ጆንሰንም ከባድ ጥያቄዎች ያቀርብልኝ ነበር።

እኔና ጺጋ ራሳችንን ከሌሎች ከከተማ ከመጡ ፈጣንና ብልጣብልጥ ከሆኑት ተማሪዎች ጋር ስናስተያይ የፈተና ውጤታችን እያስጋን መጣ። ወሬ እንዳንሆን ስለ ፈሬን ከመደበኛው የጥናት ጊዜ ውጭ በጠዋት ተነስተን በየክፍሎች ጀርባ ባሉት መብራቶች ስር ሆነን እናጠና ነበር። ብቻችንን አልነበረም የፈራነው ሌሎች የእኛ ብጤዎችም ነበሩ። አብዛኛውን ጊዜ ፋውንደሪ ሾፕ አጠገብ እናጠና ስለነበር "ፋውንደሪ" የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቶን ነበር። ቅጽል ስማችን ድብልቅ ስሜት ፈጥሮብን ሲከፋን ጺጋ "እኛ ዘመድ አዝማድ ጥለን የተሰደድነው ለትምህርት ነው፤ ያሉትን ይበሉ" በማለት ያበረታታንና ትኩረታችንን ወደ ጥናትና አላማችን ይመልሰልን ነበር።

በዚያን ዘመን በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ ሶስት ተርም ነበር። በየተርሙ መጨረሻ የፈተና ውጤት ካርድ እንደሚሰጥ፣ በከርዱም ላይ ከተማሪዎቹ ደረጃ እንደሚገለጽ ሰምተናል። ፉክክሩ በጠቅላላ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች መካከል ነበር የሚደረገው። ውጤታችንን ለማየት በናፍቆት ጠበቅን። ካርዱ ተዘጋጅቶ ሲያልቅ ወደ ዲሬክተሩ ቢሮ ሄደን መቀበል ስላለብን ብቻዬን ወደ ቢሮው ሄድሁ። ፍርሃቴ የመጨረሻ ደረጃ ማግኘት ሲሆን ከ81 የአንደኛ አመት ተማሪዎች 50ኛ ወይም 60ኛ ብሆን በደስታ ለመቀበል ዝግጁ ነበርኩ። ካርዱን ከዲረክተሩ ተቀብዬ ሳይ ዓይኔን ማመን አቃተው 9/81 የሚል ተጽፎ አየሁ፤ አላመንኩም፤ ፈነደቅሁ። በደስታ በሩጫ ወደ ዶርሚቶሪ ሄጄ ጺጋን "ካርድህን አገኘህ?" አልኩት "አዎ" አለኝ "ስንተኛ ሆንህ?" አልኩት የአንደኛ ደረጃ ተማሪ

እያለን ሁልጊዜ አንደኛ ስለሚወጣ እንደ ሚበልጠኝ እርግጠኛ ነበርኩ። በጥያቄ መለሰልኝ "አንተ ስንተኛ ሆንህ?" አለኝ። መጀመሪያ አንተ ንገረኝ መባባሉን አቆምንና "ይገርምሃል እኔ 15ኛ ወጣኹ" ሲለኝ "ይበልጥ ይግረምህና እኔም 9ኛ ሆንኹ" አልኩት፤ ውራ ባለመውጣታችን ሁለታችንም በደስታ ፈነድቅን።

ከጸጋ በደረጃ በመሻሌ ዉስጤ ኩራት ኩራት አለው። ታዲያ ኩራቱ አልበጀኝም በሚቀጥለው ተርም 21ኛ ሆንሁ:: እንዳላሽቆለቁል በርትቼ በማጥናቴ 2ኛ የሆንኹበትም ጊዜ ነበር፤ በመጀመሪያው አመት ከራዲዮ ክፍል ተማሪዎች 3ኛ በመውጣቴ ከአልጋወራሽ አስፋወሰን እንድ የራዲዮ መጽሐፍ ተሸልሜአለሁ:: ከክፍላችን 1ኛ የሚወጣው ኢዜዲን እብዶ ነበር። ኢዜዲን ወደ አሜሪካ ተልኮ ስለ ማእድን በሰፊው ተምሮ እዶላ ወርቅ ማእድን ለብዙ ዘመን በኃላፊነት ያገለገለ በኋላም በደርግ ዘመን መጨረሻው ላይ የማእድን ሚኒስትር የሆነ ነበር።

መደበኛ ትምህርታችንን ከመከታተል ጎን ለጎን እኔና ጸጋ ቅዳሜ ቅዳሜ አዲስ አበባንና ከደደር አካባቢ የመጡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የምናውቃቸውን ሰዎች ሁሉ በእግራችን እየዞርን መጎብኘት ልማድ አደረግነው፤ በእግራችን የምንዞረው የቋጠርናትን ሳንቲም ላለማውጣት መሆኑን ልብ በሉ:: ከምንጠይቃቸው ሰዎች መካከል እቴጌ መነን የልጃገረድ ትምህርት ቤት በላይ የሚኖሩትን በለጠ ወርቁንና እናቱ ይገኙበታል። አንዳንዴም ለጥቂት ደቂቃዎች ቆም እያልን ልጃገረዶቹ ወዲያና ወዲህ ሲሉ እናያቸው ነበር:: ሌላዋ የምንጎበኛት ባቡር ጣቢያ አካባቢ የምትኖር ደደር ተማሪ የነበረች ባል አግብታ ወደ አዲስ አበባ የመጣች ሴት ነበረች:: ስንጎበኛት ሁልጊዜ እረንቻታ ትጋብዘናለች:: ሲናልኮ® ለመጀመሪያ የጠጣሁት እርሷ ቤት ነው::

አንድ ቀን ልጎበኛት ሄድኹ፡ ያን ለት ግን የሰጠችኝ መጠጥ የተለየ ነበር:: ሲናልኮ መስሎኝ ፉት ስለው ጣዕሙ አንገፈገፈኝ:: ቢራ ነበር፤ ምሬት ተቋቁሜ መጠጣት ስለ አልቻልኩ ማስወገድ የምችልበትን ፈለግሁ:: ከጎረቤቶቿ ጋር ስታወራ ቆየችና ወጣ አለች:: ሚኛ ሳለሁ እንዳየሁት ወንዶች የተሰጣቸው ጠላ ሳይጣፍጣቸው ሲቀር የተቀመጡበትን ቆዳ ገለጥ አድርገው ያፈሱታል፤ እኔም እንደዛ ለማድረግ





ፈለግሁ፤ ግን ቤቱ ወለሉ በጣውላ ያማረ፣ በሰም የተወለወለ ስለነበር የማፈስበት ቦታ ቸገረኝ፣ ተጨነኩ:: ተስፋ በቆረጠ ስሜት ቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ የነበረን ልጅ "መጠጣት ትፈልጋለህ?" አልኩት፤ "እዎ" ሲለኝ "ቶሎ ቶሎ ጠጣልኝ" ብዬ ሰጠሁት:: ጭለጥ ሲያደርግልኝ ደስ አለኝ:: እርሷ ስትመጣ የጠጣ ሰው መስዬ ትንሽ ቁጭ አልኩና ተጨማሪ ግብዣ ላለመቀበል እየተግደረደርሁ ወጣሁ። ቢራ እና እኔ የመጀመሪያችንም የመጨረሻችንም ያን ቀን ሆነ::

***

እኔና ጸጋ በተግባረ እድ የትምህርት ቆይታችን ናዝሬት የለመድነውን አይነት የመጽኃፍ ቅዱስ ትምህርት ማግኘት አልቻልንም ነበር:: የሜኖናይት ሚሽዮን የሚያኪሄዱት የዕውራን ትምህርት ቤት ካዛንቺስ በሚባል ሰፈር እንዳለ ስለሰማን አፈላልገን አገኘነው:: ደርሰን ትንሽ ቆም እንዳልን አንድ ወፍራም ፈረንጅ ከግቢው ወጣ ሲሉ አየን:: ሚስተር ክላይተን ኪነር (Mr. Clayton Keener) ይባላሉ::ጠጋ እልንና ማንነታችንንና ፍላጎታችንን በአጭሩ አስረዳናቸው::

ሚስተር ኪነርም "ይህ መደበኛ የሚሽዮን ጣቢያ አይደለም፤ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለዓይነ ስውራን የከፈቱት ትምህርት ቤት ነው፤ ቢሆንም ልጆችና ሠራተኞቹ የሚካፈሉበት የእሁድ ፕሮግራም ለመጀመር አስበናል፤ ያኔ መጥታችሁ ልትካፈሉ ትችላላችሁ" በማለት አሰናበቱን:: በሳምንቱ የእሁድ ፕሮግራም ለመካፈል ጓጉተን ስንመጣ "ፕሮግራሙ የነገ ሳምንት ጠዋት ሊጀመር ነው" አሉን ይህ የሆነው ጥቅምት ወር 1945 ዓ ም መጨረሻ ነበር።

በናፍቆት የጠበቅነው እሁድ ደረሰ:: በዕለቱ በትምህርት ቤቷ ትንሽ አዳራሽ ተሰበሰብን:: የትምህርት ቤቱ ተማሪዎቹ ከፊት፣ እኛና ሰራተኞች ከተማሪዎች በኋላ፣ በግራ በኩል አንደነ አቶ ሰዩም ያሉ መምህራን ተቀመጡ:: ሚስተር ኪነር የገዙትን የመዝሙር መጽሐፍ ማንበብ ለምንችለው አደሉንና አንድ ሁለት መዝሙር ከዘመርን በኋላ ሚስተር ኪነር ዘፍጥረት አንድን መሠረት በማድረግ እንደ ለበኩ ትዝ ይለኛል:: አዲስ አበባ ውስጥ የመጀመሪዋ የመሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የዛን ቀን ተጀመረች ለማለት አደፍራለሁ::

ከዚያች ቀን ጀምሮ እሁድ እሁድ ጠዋት ወደ እዚያ እየሄድን መካፈላችንን ወደድነው፡፡ እኔ በበኩሌ በመጀመሪያዋ ዓመት መጽሐፍ ቅዱስን ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ አነበብኩ፤ "ሚሽን" የሚል ቅጽል ስምም ተሰጠኝ፡፡ የግብረ ገብነት



በመርታ ዕውራን ትምህርት ቤት ለአምልኮ ከተሰባሰቡት ጥቂቶቹ

አስተማሪአችን የቅድስት ሥላሴ ሥነ መለኮት ኮሌጅ ምሩቅ ሲሆን ብዙ ጥያቄ ከሚያቀርቡለት ተማሪዎች አንዱ ነበርኩ፡፡ ስለ ጸድቃን አማላጅነት፣ ስለ ጾም፤ ቅዳሴ በማይገባን ቋንቋ በግእዝ ለምን ይሆናል? የሚሉት ጥያቄዎችን አንደ እነሳሁበት ትዝ ይለኛል፡፡

***

የሚገርመው ነገር ከሜኖናይት ሚስዮን ፕሮግራም በተጨማሪ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ወደ ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን ሄደን ከእቴጌ መነን ና ከሌሎችም ት/ቤቶች ከመጡ ወጣቶች ጋር ስብከት እንከታተል ነበር። በክቡር አቶ አካለወልድ የተምህርት ሚኒስቴሩ መሪነት የሃይማኖተ አበው ማኅበር የተጀመረው ያኔ ነበር። እሁድ እሁድ ደግሞ ሞግዚታችን በጠዋት በየመኝታ ክፍላችን እያንኳኩ «ተነሱ፣ ወደ ቤተስኪያን ሂዱ ይሉን ነበር»፤ እኛም በየማለዳው ልደታ እየሄድን እናስቀድስ ነበር፡፡ እንደ ገና ከቅዳሴ መልስ ቁርስ በልተን ወደ ካዝንቺስ ሄደን ከመጽሐፍ ቅዱስ ስብከት ሰምተን እንመለሳለን። እስከ ሚለይልን ድረስ ሁለቱን ሥርዓተ አምልኮዎች እያቻቻልን ዓመቱን አገባደድነው። የዓመቱን ማጠቃለያ ፈተና ወስደን ለክረምት እረፍት የምንለቀቅበትን ናፈቅን።





## የመጀመሪያ የእረፍት ጊዜ

በአውነቱ የመጀመሪያ አመት የተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ቆይታዬ ረዝሞብኝ ነበር፡፡ በአመቱ መጨረሻ በችግረኝነት[2] (free supply) የተመዘገቡ ተማሪዎች ወደ ቤታቸው መመለሻ ገንዘብ ይሰጣቸዋል፡፡ እኔና ጸጋ ግን ይህ ዕድል አልነበረንምና መመለሻ ገንዘብ ቤተሰቦቻችን እንዲልኩልን መልእክት ላክን። ገንዘቡ ጉዞ ልንጀምር ላሰብንበት ቀን (ሰኔ 30) ለእኔ ሳይደርስልኝ ቀረ፡፡ ይህ ሁኔታ መጀመሪያም የረዘመብኝን ዓመት ይበልጥ እንዛዛው፡፡ ትምህርት ቤቱ ውስጥ መቆየት የሚቻለው እስከ ሐምሌ 16 ብቻ ስለነበር ወደ አባቴ የቅርብ ጓደኛ አቶ ተከለማርያም ሄጄ ችግሬን መናገር ግድ ሆነብኝ። እርሳቸው መጓጓዣ ሰጡኝና የደደር ጉዟችንን በቃላት ሊገለጽ በማይችል ደስታ ተሞልተን ጀመርን፡፡

ደደር እንደ ደረስን ከወላጆቼ አስገራሚ ጥያቄ ቀረበልኝ፡፡ አባቴ "ትምህርት ቤት የተዘጋው ሰኔ 30 ነው፤ ለምን ዘገያችሁ?" አለኝ፡፡ ከግርምቴ ሳልወጣ "ለምን መመለሻ ገንዘብ አልላካችሁልኝም" በማለት መለስኩለት፡፡ የእባቴ ፊት ላይ የድንጋጤ፣ የግርምትና የንዴት ስሜቶች በፍጥነት ከተፈራረቁ በኋላ በሃዘን ድምጽ "በአገሌ እጅ ነበር የመጓጓዥ ገንዘብ የላኩልህ ይሄ አታላይ እንዴት አልሰጠህም?" አለ። ገንዘብ ተልኮ እንደነበር ስሰማ ተፈጥሮብኝ የነበረው ቅሬታ ተወገደ፡፡

ገንዘቡን የወሰደብኝን ሰውዬ ማንነት ሳውቅ በጣም ታዘብኩት፤ ምክንያቱም ሰውዬው ውለታዬ ያለበት ሰው ነበር፤ ይህ ሰው አንድ ቀን አደን ሄዶ ድኩላ ያገኘ መስሎት በስህተት ሰው ገደለ፤ ወደ ሙጢ ሸሽቶ ጀምሮ ሌሊት ሐሪርቲ መጣ፡፡ ከእኛ ቤት እስከ ሙጢ መንገዱን የመራሁት እኔ ነበርኩ። የእባቴን እደራና የኔን ውለታ መብላቱ እስገረመኝ፡፡

የክረምት ወራት እረፍታችንን (በድሮ አነጋገር) 'ካገር ወደ እገር' በመዘዋወር ነበር ያሳለፍነው፡- ሚኛ፣ ደሩ፣ መንዲሳ፣ ለገገበ፣ ከራባ ጡሎ ሂርና ሄደን ነበር፡፡ ከሁሉም ግን የጡሎው ጉዞ ረጂም ነበር፡፡ ወደ ጡሎ የሄድነው ጸጋ፣ አሸብርና

እኔ ሆነን ነው፤ ዝምድናው ትንሽ ራቅ ይበል እንጂ ለካ ከጸጋ ጋር የጋብቻ ዝምድና ነበረን፡፡ ያ የጋራ ዘመዳችን ያለው ጡሎ ስለነበር እብረን የመሄድ እድል አገኘን።

ጡሎ ደደርን አልፎ፣ ደሩ ማርያምን በስተ ግራ ተመልከተን ቡርቃን እቋርጠ የሚኬድ የአንድ ቀን ጉዞ ነበር። ለሶስታችን ሁለት በቅሎች ነበሩን፡፡ ከደደር በጠዋት ፀሐይ ስትወጣ ተነስትን ሁለቱ በቅሎዎች ላይ በፈረቃ በመውጣት ስንጓዝ ዋልን። ለሁለት ወይም ለሶስት ሰዓት ያህል ከተጓዝን በኋላ ወንዝ አጠገብ ስንደርስ ወርደን በቅሎዎቻችንን ውሃ እናጠጣለን፤ አግራችንን እንታጠብና እንቀጥላለን፤ ባለ ጫማ እኔና ጸጋብቻ ነበርን። የእኔ የሸራ ጫማ ናት፤ በቅሎዋ ላይ መውጣት ተረኛ ከሆንሁ ሸራ ጫማዬን አጥቤ ጫማዬን እድርጌ በቅሎ ላይ አወጣና አደርቀው ነበር፡፡ ጡሎ የሄድንበት ተጨማሪ ምክንያት መእዛ የምትባለዋ የአለከስቴ ልጅ ለሁለተኛ ጊዜ እግብታ ለመልሱ ነበር፡፡ ብዙ ተጫወትን፣ ዘፈንን፣ ደለቅን፡፡

ሦስት ቀን ጡሎ ከቆየን በኋላ በጣም የምወዳትን የአከስቴን ልጅ ደብሬንና ቤተሰቧን ለመጠየቅ ወደ ሂርና ተጓዝን፡፡ ከጡሎ ሂርና የግማሽ ቀን ጉዞ ነበር፡፡ ሂርና ከመግባታችን በፊት ተጣጥበንና ዘንጠን መግባት ስለፈለግን እንደ ልማዳችን ከበቅሎዎቻችን ወርደን ሂርና ልንደርስ ቲኒሽ ሲቀረን ባየናት ወራጅ ወንዝ ተጣጠብን፡፡ እኔም ሸራ ጫማዬን እጥቤ የጫማ ማሰሪያዎችንም ለማለቅለቅ ወደ ወንዙ ውስጥ ነክርኩትና አወጣሁት፡፡ ከው አልኹ፤ ደነገጥኹም። ለካ የሁለቱን ማሰሪያዎች ጫፍና ጫፍ የያዝሁ መስሎኝ ያንዱን ጫፎች ብቻ ይዤ ነበር ከወንዝ ውስጥ ያወጣሁት፡፡ የአንድ አግሩ ከር ተወሰደብኝ፡፡ በፍሊጋው እንዲረዱኝ አሸብርና ጸጋን ጠራኋቸው፤ ወንዙን ተከትለው የጫማ ከሬን ሊያገኙልኝ ሞከሩ፣ አልተቻላቸውም፡፡

በጫማ ዘንጦ የመታየት ዕድሌን ማጣት ስላልፈለኩ ብቻዬን ፍለጋዬን ቀጠልሁ። እካሄዱን ለማየት ብዬ በአጀ ላይ የቀረቺውን ማሰሪያ ወንዙ ላይ ጣል እደረግኋት፤ እርሷም ስመጠች፤ ተንሳፋ ለማየት ብዙ ጠበቅኹ፤ ስጥማ ቀረች፤ ተስፋ ቆረጥኩ፡፡ ከዚያማ ጫማዬን በግቻ አስሬ ከተማ ገባሁ፤ ጫማ ማሰሪያ





ፈልጌ ስላላገኘሁ ሶተሉ ገዝቼ አስሬ ወደ ደብሬ ቤት ሄድን።

ደብሬ ቤት እንደደረስን መልካም አቀባበል ተደረገልን፡፡ ደብሬ ግሩም ባለሙያ ነች፤ ቁርስ አበላችን፤ ወዲያው ጋሼ ተፈራ ፍየል አረደ፤ ከእኛ ጋር እየተጫወተች ዱለቱም ተዘጋጀ፤ ወጡም ተሰራ፤ ግሩም እራት በላን፤ በማግስቱ ወደ ጡሎ ተመለስን። ደብሬን ለመጨረሻ ጊዜ ያየኋት ያኔ ነበር።

በማግስቱ ወደ ጡሎ ከዚያም ወደ ደደር ተመልሰን በየፊናችን ዘመዶቻችንን መጠየቅ ቀጠልን። በእረፍት ቆይታችን ወቅት እኔና ፀጋን ያስደሰተን ነገር ደደር ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ፈተናን ያለፍን የመጀመሪያ ወጣቶች በመሆናችን ከደደር ወጣቶች የምናገኘው የአድናቆት አይታ ነበር። በምንንቀሳቀስበት ቦታ ሁሉ በአድናቆት ይመለከቱን ነበር፡፡ የእረፍት ጊዜአችንን ጨርሰን ወደ አዲስ እበባ ለመመለስ ኩሬራችንን (የጊዜው አውቶቡስ) ለንሳፈር ሸኘዎቻችን እምና አንዳለቀሱት በአንባ ላይሆን በደስታ ነበር የሸኙን፡፡